# ኤዱኬሽን ፎር ሰስተነብል ዲቨለፕመንት

## ሞጁል ዘጠኝ

# የሙዚቃ ትምህርት
# Preschool Music



## የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን ስልጠና ሞጁል

ጥቅምት 2004 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ESD

# ኢዱኬሽን ፎር ሰስተነብል ዲቨለፕመንት

## የሙዚቃ ትምህርት

## Preschool Music

## የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን ስልጠና ሞጁል

አማካሪ፡ ፍሮምሲስ የትምህርት ስልጠና አ.ማ

አዘጋጅ ፡ ብርሀኑ ቦንጋ

ESD

# ምስጋና

ይህ ሞጁል የተዘጋጀዉ በፍሮምሲስ የትምህርትና ስልጠና አ.ማ እና በኢዱኬሽን ፍር ስስተነብል ዲቨለፕመንት ትብብር ሲሆን ለዚህም ማህበሩ ለኢዱኬሽን ፍር ስስተነብል ዲቨለፕመንት ከፍ ያለ ምስጋና ያቀርባል፡፡ በተለይም በፍሮምሲስ የትምህርትና ስልጠና አ.ማ ስር ሆነዉ በሞጁል ዝግጅትና በስልጠ በየሞያ ዘርፋቸዉ አስተዋፅኦ ያደረጉትን ባለሙያዎች ከልብ ያመሰግናል ፡፡

በመጨረሻም የኢዱኬሽን ፍር ስስተነብል ዲቨለፕመንት ሰራተኞች ለስልጠናዉ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን በማስተካከል ስልጠናዉ የተሳካ እንዲሆን ላደረጉት አስተዋፅኦ ማህበሩ ምስጋናዉን ያቀራባል፡፡

# ማውጫ


መግቢያ ........ v

ምዕራፍ 1 ........ 1

ሙዚቃ ምንድው? ........ 1

የሙዚቃ ቲዮሪ (ንድፈ ሀሳብ) ........ 4

ምዕራፍ 3 ........ 12

የሙዚቃ ታሪክ ትምህርት ........ 12

ምዕራፍ 4 ........ 22

የሙዚቃ መሳርያዎች ........ 22

ምዕራፍ 5 ........ 28

የኢትዮጵያ ሙዚቃ ዜማዎችና ቅኝቶች ........ 28

ምዕራፍ 6 ........ 30

ሶልፌጆ ........ 30

ምዕራፍ 7 ........ 33

ሙዚቃ ለህፃናት ያለው ጠቀሜታ ........ 33

ምዕራፍ 8 ........ 35

የሙዚቃ ስሜት እድገት በህፃናተ ከልደት እስከ ስድስት አመት ........ 35

ምዕራፍ 9 ........ 37

የቅድመ መደበኛ የሙዚቃ ትምህርት ዓላማናይዘቶች ........ 37

አባሪ 1፡ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ናሙና መዝሙሮች ........ 43

አባሪ 2፡- የየምዕራፎቹ ጥያቄዎች መልስ ........ 48

ዋቢ መፅሀፍት (Referances) ........ 51

# ኮርስ አውትላይን

የኮርሱ ዓላማ ÷ ከዚህ ትምህርት በሆላ እጩመምህራን

1. ስለ ሙዚቃ ሳይንሳዊ ጥበብ መጠነኛ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡
2. የሙዚቃ አፃፃፍና አነባበብን አውቀው ለህፃናት ሚሆኑ ቀላል ሪትሞችን ማስተማር ይችላሉ፡
3. ስለ ኢትዮጵያ ሙዚቃ የዜማ አመሰራረት ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡
4. የአጸደ ሕጻናት የሙዚቃ ትምህርት ዓላማና ይዘትን ተገንዝበው ለህጻናት የሚሆኑ የሙዚቃ ትምህርት የመምረጥ የማዘጋጀትና የማስተማር ልምድ ይኖራቸዋል፡፡
5. የሙዚቃ ትምህርት ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለውን ግንኙነት በመገንዘብ ትምህርቱን በቅንጅት ማስተማር ይችላሉ፡፡

የኮርሡ ይዘቶች

1. ሙዚቃ ምንድነው?
   - 1.1 የሙዚቃ ትርጉም
2. የሙዚቃ ንድፈ ሀሳብ ትምህርት
   - 2.1 የሙዚቃ አናባቢ ፊደል (ኖታ)
   - 2.2 የሙዚቃ መፃፍያ ሰሌዳ(ስታፍ)
3. የሙዚቃ ድምፆች
4. የሙዚቃ ታሪክ ትምህርት
   - 4.1 የሀገር ውስጥ
   - 4.2 የውጭ ሀገር
5. የሙዚቃ መሳርያዎች
   - 5.1 የሙዚቃ መሳርያዎች ዓይነት

6. የኢትዮጵያ ሙዚቃ ዜማዎችና ቅኝቶች

7. ሶልፌጆ

7.1 የሶልፌጆ ትርጉም

7.2 ቀላል ኖታዎችን ማንበብና መፃፍ

8. የሙዚቃ ስሜት ዕድገት በህጻናት

9. የሙዚቃ ትምህርት ለህጻናት ያለው ጠቀሜታ

10. የቅድመ መደበኛየሙዚቃ ትምህርት ዓላማ

11. የቅድመ መደበኛ የሙዚቃ ትምህርት ይዘቶችና ናሙና መዝሙሮች

## መግቢያ

ሙዚቃ የሰውን ስሜት መግለጫ ከሆኑት የስነጥበብ ዘርፎች አንዱ ነው፡፡የሰው ስሜት መግለጫ ነው ሲባል ስሜትን በመቀሰቀስ በድምፅ አማካይነት ሰዎች ትዝታቸውን፤ሀዘናቸውን፤አንድነታቸውን፤ብሶታቸውን ወዘተ… የሚገልፁበት ነው፡፡

ይህ የትምህርት ሂደት ኪነታዊ እውነታ ኖሮት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ kንቋን ተፈጥሮን፤አካባቢን ወዘተ…በቀላሉ ለመገንዘብና ለማወቅ አስተማሪነቱ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡በመሆኑም ጥበቡን ለማስፋፋትና ተግባራዊ ለማድረግ መምህራን በቅድሚያ ትምህርቱን መማርና ማወቅ ስለሚኖርባቸው ለዚሁ ስልጠና ይረዳ ዘንድ ከቅድመ መደበኛ መምህራንማሰልጠኛ ተቋም አላማ አንፃር ሲለበሱ ተዘጋጅቶ የማስተማርያ ፅሁፉም ከዚሁ ጋር ቀርቧል፡፡

የሚያካትተው ይዘትም የሙዚቃ ንድፈ ሀሳብን፤ሦልፌጅን፤መዝሙርና እንቅስቃሴን፤የሙዚቃ መሳርያዎችን ሲሆን በአብዛኛው ህፃናት በቀጥታ ከሚማሩትና ይህንን እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው የሚያተኩር ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ 1

## ሙዚቃ ምንድው?

ዓላማ፡-

- የሙዚቃን መሰረታዊ ትርጉም ይረዳሉ
- ስለ ሙዚቃ ድመፅ ባህርያት ያውቃሉ
- የሰዎች ድምፅ አመዳደብን ይረዳሉ

### ሙዚቃ ምንድነው?

ሙዚቃ የሚለው ቃል የመጣው ሙዚክ (musike)ከተባለ የግሪክ ቃል ሲሆን ይህንኑ ቃል ግሪኮች በኪነጥበብ ስም ለሰየሚቸው ሚዩዚክ ለተባሉ ዘጠኝ አማልክት ከተሰጡት ስም የተወሰደ ነው፡፡አጠቃቀሙም ለሁሉም የኪነጥበብ ዘርፎች የተሰጠ ስም ነበር፡፡ይህውም ቃል በመሸሻል ሙዚቃ (Musica)በሚባል ተለወጠ፡፡

ሙዚቃ የልዩ ልዩ ድምፅና ምት ስነጥበባዊ ቅንብርውጤት ነው፡፡እንዲሁም ሙዚ ቃ ሳይንስም ኪነጥበብም ነው፡፡ ይህም ሲባል ስሜትንና ሃሳብን በሙዚቃ አማከይነት በመግለፅ ረገድ በኪነጥበብነቱ ስንመለከተው የድምፅን ርግብግቢት መጠንና ቃና በመለካት ረገድ ድግሞ ስንወስደው ሳይንሳዊነቱን ያረጋግጣል፡፡ለምሳሌ ፊዚክስ የቫዮሊን የክር መሳርያ ድምፅ ከቤዝ የሙዚቃ መሳርያ ድምፅ ለምን ከፍተኛ እንደሆነ ሲያስረዳን፤ ከኬሚስትሪ ጋር ደግሞ የኮፐርንና የዚንክን መጠን ለትራንፔት የትንፋሽ ሙዚቃ መሳርያ ምን ያህል እንደሚያስፈልገ ይጠቁመናል፡፡

ሙዚቃ በአለማችን ለሚገኙ ህይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ በተለይም ለሰው ልጆች የእለት ተእለት የህይወት ገጠመ ኞች ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በመግባት ሙዚቃ ለህዘን፤ለደስታ፤ለፍቅር፤ለስራ ወዘተ… መግለጫነት የሚያገለግል የኪነጥበብ ዘርፍ ነው፡፡ሙዚቃ የሰው ልጅ ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ የነበረና ከሰው ልጅ የእድገት እርምጃ ጋር አብሮ ሲጓዝ የቆየ ነው፡፡

ሙዚቃ ማለት መሰረቱ ድምፅ ሆኖ ሙዚቃ ማለት ድምፅን አቀነባብሮና አዋህዶ ለጆሮ የሚጥም ድምፅን የመፍጠር ጥበብ ሲሆን በውስጡም ሙዚቃን ሙዚቃ የሚያሰኙት ድምፅ(Sound) ዜማ(Melody) ህብረ ድምፅ (Harmony) ምት (Rhythm)በውስጡ የያዘ ነው፡፡

## ድምፅ(sound)

ድምፅ ማለት ማንኛውም በአካባቢያችን የምንሰማው ነገር ሲሆን የሚፈጠረውም በግጭት፤በንዝረትና በመሳሰሉት ሊፈጠር ይችላል፡፡እነዚህ የምንሰማቸው ድምፆችም በሁለት ይከፈላሉ፡፡ አንደኛው የድምፅ ዓይነት የሙዚቃ ድምፅ የምንለው ሲሆን የሙዚቃ ድመፅ በተስተካከለ የአየር ርግብግበት የሚንዝና ለጆሮ ትርጉም ሊሰጥ የሚችል የሚስማማ ነው፡፡ለምሳሌ የዋሽንት ድምፅ፡፡

ሁለተኛው ሁካታ ተብሎ የሚጠራውና ባልተስተካከለ የአዩር ርግብግበት የሚንዝና ለጆሮ ትርጉም የማይሰጥ የማይስማማ ድምፅ ነው፡፡ለምሳሌ የሁለት መኪናዎች ግጭት፡፡

የሙዚቃ ድምፅ መለያ በህርያት አምስት ናቸው፡፡አነሱም፡-

1. **ቅኝት (pitch)** የድምፅ ከፍተኛነትና ዝቅተኛነትን ያመለክታል፡፡ ለምሳሌ የተወጠረ ላስቲክና ያልተወጠረ ላስቲክ፡፡
2. **የድምፅ ቀለም (tone colour)** ድምፅን በማድመጥ ብቻ በጆሮአችን የምንለይበት ነው፡፡ለምሳሌ የሴትን ድምፅ ከወንድ ድምፅ፤የዋሽነትን ድምፅ ከጊታር ድምፅ ወዘተ...
3. **የድምፅ ቃና (tone quality)** የሙዚቃ መሳርያም ሆነ የሰውም ድምፅ የራሱ የሆነውን ውስጣዊ ውበት የምንገልፅበት ነው፡፡ ለምሳሌ -- የዋሽንት ድምፅ ውበት፤የበገና ድምፅ ውበት ወዘተ...
4. **የድምፅ ቆይታ (duration)** የአንድን የተወሰነ ድምፅ መርዘም ወይም ማጠርን ያመለክታል፡፡
5. **የድምፅመጠን (Volume)** የድምፅ ልስላሴ ወይም መጮህን ያመለክታል፡፡ለምሳሌ በሀይል የተመታ ፒያኖ ድምፅ፤ በማለስለስ የተመታ የፒያኖ ድምፅ ወዘተ...

## ዜማ (Melody)

ዜማ ማለት ተከታታይነትን የያዙና ዝምድና ያላቸው ሊማርኩ የሚችሉ ድምፆች ስብስብ ነው፡፡የድመፅ ቅላፄ (SWETABLE SOUND) ማለት ነው፡፡

## ህብረ ድምፅ (harmony)

ህብረድመፅ ማለት ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ የተለያዩ ድምፆችን ውህደት ያመለክታል፡፡ ከዚህ በመነሳት የሰዎች ድመፅወሰን (voice range) በአራት ይመደባል፡፡ እነሱም÷

1. ሶፕራኖ (soperano)
2. አልቶ (alto)
3. ቴነር (tenor)
4. ቤዝ (bass) ናቸው፡፡

ሶፕራኖና አልቶ በአማካይ የሴቶች ድምፅ ክፍል ሲባሉ ቴነርና ቤዝ ደግሞ በአማካይ የወንዶች ድምፅን ያካትታሉ፡፡

## ምት (Rhythm)

ሙዚቃን ሙዚቃ ከሚያሰኙትና ተደማጭ ከሚያደርጉት አንዱና ዋናው ሪትም ይሆናል፡፡

የሙዚቃ ድመፅ የጊዜ ቆይታ ያለውን የጊዜ ርዝማኔ የሚያመለክቱ የተለያዩ መገለጫዎች አሉት፡፡ድመፅ የሚቆይበት ጊዜ በትክክል ሊለካ ይችላል የቀን የገዜ መጠን የሚለካው በሰአት እንደመሆኑ መጠን የድምፅ ቆይታውም የሚለካው በምት ይሆናል፡፡ሪትም በአጠቃላይ የሙዚቃውን ፍጥነትና ዝግታ አንደሜትር ሆኖ የሚለካና አጠቃላይ የሙዚቃው እንቅስቃሴ የሚገለፅበት ነው፡፡

**የማነቃቅያ ጥያቄዎች**

1. የሙዚቃ መሰረቱ ምንድ ነው?
2. የድምፅ መለያ በህርትያትን ዘርዝሩ
3. አንድን ላስቲክ በረጅሙ በመወጠርና በማላላት ያለውን ድምፅ ልዩነት ግለፁ
4. የሰዎች ድምፅ በስነት ይከፈላል አይነታቸውን ጭምር ግለፁ

# ምዕራፍ 2

## የሙዚቃ ቲዮሪ (ንድፈ ሀሳብ)

**ዓላማ ሰልጣኞች ከዚህ ትምህርት በሆላ÷**

- ✓ ሙዚቃ የሚፃፍ የሚነበብ መሆኑን ይረዳሉ
- ✓ የሙዚቃ ድምፆችን ይተዋወቃሉ

## የሙዚቃ ቲዮሪ (ንድፈ ሀሳብ)

ሙዚቃ እንዴት እንደሚፃፍና እንደሚነበብ ትምህርት የምናገኝበት የሙዚቃ ዘርፍ የሙዚቃ ቲዮሪ ትምህርት ነው ፡፡

በዚህ ክፍል የምንማረው፡-

- የሙዚቃ አናባቢ ምልክቶች (ኖታ)
- የሙዚቃ መፃፍያ ሰሌዳ (ስታፍ)
- የሙዚቃ ድምፆችን
- ሙዚቃን ለማንበብ የሚረዱ ምልክቶችን
- ክሌፍ
- የጊዜ መለኪያ ምልክቶችን ያካትታል፡፡

**የሙዚቃ አናባቢ ምልክት (ኖታ)**






የሙዚቃ ድምፅ የሚነበብበት ምልክት ኖታ በመባል ይጠራል፡፡

ኖታ በሁለት ይከፈላል፡-





1. የድምፅ ኖታ
2. የእረፍት ኖታ በመባል፤

የድምፅ ኖታ የሙዚቃ ድምፅ በስራ ላይ የሚቆይበትን የጊዜ ቆይታ የሚያመለክት ነው፡፡

## 1.የድምፅ ኖታ

| ኖታው | የኖታው መጠርያ ስም | የጊዜ ቆይታ ዋጋው |
|---|---|---|
|  | ሙሉ ኖታ | 4 ምት የድመፅ ቆይታ |
|  | ግማሽ ኖታ | 2 ምት የድምፅ ቆይታ |
|  | እሩብ ኖታ | 1 ምት የድምፅ ቆይታ |
|  | አንድ ስምንተኛ ኖታ | ግማሽ ምት የድምፅ ቆይታ |
|  | አንድ አስራስድስተኛ ኖታ | እሩብ ምት የድምፅ ቀይታ |


## 2. የእረፍት ኖታዎች

| | | |
|---|---|---|
|  | ግማሽ የእረፍት ምልክት | ሁለት ምት የእረፍት ቆይታ |
|  | እሩብ የእረፍት ምልክት | አንድ ምት የእረፍት ቆይታ |
|  | አንድ ስምንተኛ የእረፍት ምልክት | ግማሽ ምት የእረፍት ቆይታ |
|  | አንድ አስራ ስድስተኛ የእረፍት ምልክት | እሩብ ምት የእረፍት ቆይታ |


<u>**ስታፍ ( Staff)**</u> ስታፍ ማለት አምስት ወደ ጎን የተሰመሩ መስመሮችና በመስመሮች መሀከል አራት ክፍት ቦታዎች ያሉት የሙዚቃ መፃፍያ ሰሌዳ ነው፡፡

የሙዚቀ ድምፆችን በኖታ ለመፃፍ የስታፍ መስመሮችና ክፍት ቦታዎች እኩል የሆነ አገልግሎት አላቸው፡፡

ይህ ስታፍ ነው፡-




የስታፍ መስመርና ክፍት ቦታዎች መለያ ቀጥር አላቸው፡፡ መለያ ቁጥር የሚሰጣቸው ከታች ወደ ላይ ነው፡፡




**ክሌፍ (Clef)** ክሌፍ ማለት በስታፍ በስተግራ መነሻ ላይ የሚቀመጥ የሙዚቃ ምልክት ሲሆን አገልግሎቱም በስታፍ ላይ የሚፃፉ የሙዚቃ ድምፆች የመስመርና የክፈት ቦታዎችን መጠርያ ስያሜ ያመለክታል ስለዚህ በክሌፍ አማከኝነት የሙዚቃ መፃፍያ ሰሌዳው(ስታፍ)መጠርያ ስም ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡

መሰረታዊና ዋናዎቹ የከሌፍ አይነቶች ሁለት ናቸው እነሱም

1. ትረብል ክሌፍ (G Clef) የቀጭን ድምፅ መገልገያ ቁለፍ



2. ቤዝ ክሌፍ ( F Clef) የወፍራም ድምፅ መገለገያ ከቁልፍ



## የሙዚቃ ድምፆች

መሰረታዊና ዋናዋናዎቹ የሙዚቃ ድምፆች ሰባት ናቸው እነዚህ ድምፆች የየራሳቸው የሆነ ሁለት አይነት መጠርያ ስም አላቸው፡፡


እነርሱም

| በጣልያንኛ | ዶ | ሬ | ሚ | ፋ | ሶል | ላ | ሲ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በእንገሊዝኛ | C | D | E | F | G | A | B |


የጣልያንኛው ስያሜ ድምፆችን በማውጣት ለመዘመር የምንገለገልበት ሲሆን የእንገሊዝኛውን ፊደል የስታፍን መስመርና የክፍት ቦታዎችን ስያሜ ለመተዋወቅ እንጠቀምበታለን፡፡

የሙዚቃ ድምፆች የእጅ ምለክት

ሰባቱን ዋናዋና የመዚቃ ድምፆች በተለይ ለህፃናት በቀላሉ ለማስተማር እነዲመች የእጅ ምልክቶች ተዘጋጅቶላቸዋልዋል፡፡ ይህ የሙዚቃ ድምጾችን የማስተማርያ ዘዴ የተዘጋጀው ዞልቶንኮዳይ በተባለው የሀንጋሪ ተወላጅ ሲሆን የማስተመርያ ዘደውም ዞልተን ሜቶድ በመባል ይታወቃል፡፡ምልክቶቹም የሚከተሉት ይሆናሉ





የመዚቃ ድምፆች በፒያኖ ላይ ያላቸው አቀመቀመጥና መጠርያ ስማቸው ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡




የመስመሮችና የክፍት ቦታዎች አጠራር በስታፍ ላይ


## በትረብል ክሌፍ(G Clef)የመስመርና የክፍት ቦታ መጠርያ ስም




የትረብል ክሌፍ የመስመሮችን ስም ለማስታወስ Every - Good - Boy - Does – Fine

የትረብል ክሌፈ የክፍት ቦታዎችን ስም ለማስታወስ F - A - C - E

## በቤዝ ክሌፍ(F Clef) የመስመርና የክፍት ቦታዎች መጠርያ ስም




የቤዝ ክሌፍ የመስመሮችን ስም ለማስታወስ **G**ood – **Boy** - **D**oes - **F**ine- **A**lways

የቤዝ ክሌፍ የክፍት ቦታዎችን ስም ለማስታወስ **A**ll - **C**ows - **E**at - **G**rass.

## የጊዜ መለኪያ (time signature)

የጊዜ መለኪያዎች (Time signature) ማለት በስታፍ ላይ ከክሌፍ ቀጥሎ የሚቀመጥ ክፍልፋይ መሰል ቁጥር ሲሆን በሙዚቃ ንባብ ውስጥ የሚሠጠው አገልግሎት

ሀ.በኖታ የሚፃፉ ሙዚቃዎች በእያንዳንዱ የስታፍ የኖታ ክፍል ውስጥ የሚኖረውን የምት መጠን ማመልከትና

ለ. በእያንዳንዱ የስታፍ የኖታ ክፍል ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸውን የኖታ አይነቶች ማሳወቅና፡፡

ቀላልና መሰረታዊ የጊዜ አመልካች የሚባሉት፡- 4 3 2

4 4 4 ናቸው

የጊዜ መለኪያን ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉት ይኖራሉ

1. መክፈያ መስመር( Bar line)
2. መዝጊያ መስመር (Double bare line)
3. የኖታዎች ምድብ ቤት ( Bar)

1. መክፈያ መስመር ( Bar line) ማለት በሚሰጠው የጊዜ መለኪያ ቁጥር መሰረት ኖታዎችን እኩል በእኩል የሚከፋፈል አንድ ቀጥተኛ መስመር ነው፡፡

2. መዝጊያ መስመር(Double bare line) ማለት ከኖታዎች ድርደራ በስተመጨረሻ ለመዝጊያነት የሚያገለግል ሁለት ቀጥተኛ መስመር ነው፡፡


3. የኖታዎች ምድብ ቤት (Bar)ማለት ኖታዎች ተከፋፍለው የሚገኙበት ምድብ ቤት ነው፡፡

**አጠቃላይ ምሳሌ ፡**



**የሙዚቃ መፃፍያ አጠቃቀም**

**የሙዚቃ መፃፍያ ሰሌዳ መሰረታዊ አጠቃቀም ከዚህ እንደሚከተለው የሆናል።**




**የማነቃቅያ ጥያቄዎች፡-**

1. የሙዚቃ አናባቢ ፊደል ምን ይባላል?
2. የሙዚቃ መፃፍያ ሰሌዳ ስንት መስመርና ክፍት ቦታዎች አሉት?
3. ዋናዋናዎቹ የሙዚቃ ድምፆች ስንት ናቸው ስማቸውን ጭምር ጥቀሡ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ሀሰት በማለት መልሡ**

4. የሙዚቃ ድምፆች ብዛት አይታወቅም
5. መሰረታዊና ዋናዎቹ የሙዚቃ ድምፆች ሰባት ናቸው
6. እያንዳንዱ የሙዚቃ ድምፅ ሁለት ሁለት መጠርያ ስሞች አሉት
7. በፒያኖ ላይ የሙዚቃ ድምፆች አቀማመጥ ነጭና ጥቁር ነው
8. ሙሉ ኖታ አራት ምት የድምፅ ቆይታ አለው

# ምዕራፍ 3

## የሙዚቃ ታሪክ ትምህርት

**ዓላማ ሠልጣኞች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-**

- ✓ የሀገራችንን ጥንታዊና መሰረታዊ የሙዚቃ ምንነትን ይረዳሉ
- ✓ የኢትዮጵያን የዘመናዊ ሙዚቃ አነሳስና እንቅስቃሴ ይረዳሉ
- ✓ የሀገራችንና አለም አቀፍ ታላላቅ የሙዚቃ ደራስያንን ይተዋወቃሉ


### የሙዚቃ ታሪክ

### የሀገር ውስጥ ሙዚቃ

ስለ ኢትዮጵ ሙዚቃ ሲነሳ የቅዱስ ያሬድ ስም መነሳቱ አይቀሬ ነው፡፡ስለሆነም የሀገራችንን የዘመናዊ ሙዚቃ የእድገት መነሻ ከመመልከታችን በፊት የያሬድን የመዚቃ ፈጠራ ባጭሩ እናያለን፡፡

ያሬድ በ505 ዓ.ም በአክሱም ተወለደ አባቱ የስሀቅ እናቱ ክርስቲና ይባላሉ፡፡በዚያን ጊዜ የነበረው የአክሱም ንጉስ ንጉስ አፄ ካሌብ ነበር፡፡

የያሬድን ሙዚቃዊ ፈጠራዎችን በሦስት ዋና ክፍሎች ለማየት ያህል



1. ያሬዳዊ የዜማ ስልቶች (ቅኝት) ሶስት ናቸው፡፡

እነሱም ፡-

1. ግእዝ
2. እዝል
3. አራራይ ናችው፡፡

2. ያሬዳዊ የድምፅ መመርያ ምልክቶች በቁጥር ስምንት ናቸው፡፡

እነሱም፡-

| | |
|---|---|
| 1.ደረት | 5. ቅናት |
| 2. ይዘት | 6. ጭረት |
| 3. አራራይ | 7. ቁርጥ |
| 4. ርክርክ | 8. ድፋት |

ተብለው ይጠራሉ፡፡

ያሬድ የተለያዩ የዜማ መፅሀፍትን ፅፏል ከነዚህም ውስጥ አንዱና ዋናው ድጓ በመባል ይታወቃል፡፡

ያሬድ የኖረበት ዘመን ከ505 ዓ.ም እስከ 571 ዓ.ም ነበር፡፡

የሙዚቃ እድገት ከፍ እያለ ሲሄድ ሙሉ በሙሉ ከመንፈሳዊ አገልሎት ወደ አለማዊነት ሲለወጥ የኢትዮጵያ ሙዚቃም በአንፃሩ በቂ ፅሁፍና ማስረጃ ባይገኝም በአንዳንድ መረጃዎች እንደምናየው ኢትዮጵያ ከውጭ ዓለም ጋር ግንኙነት ከጀመረችበት አንስቶ የውጭ ዜጎች ወደ ሀገራችን በንግድ፣ በኑዋሪነት፣ በቱሪስትነት በመሳሰሉት መልኩ የሌላው አለም ስልጣኔ ይዘው ሲገቡ የዘመናዊ ሙዚቃ መሳሪያዎችም በቅንብር ውጤቶችና ስልቶቻቸውን ይዘው መጥተዋል፡፡

ለምሳሌ በ1996 ዓ.ም በተለያየ ሙያ ሰልጥነው ከገቡት አርባ የአርመን ተወላጆች መካከል የሙዚቃ እውቀት ያላቸው ስለነበሩ የዘመናዊ ሙዚቃ ጥበብ ለማሳወቅና ለማስፋፋት ጥረት አድርገዋል፡፡ በነዚህም የአርመን የሙዚቃ ባሙያዎች አነሳሽነትም በድሮው ክብር ዘበኛ

ውስጥ ሙሴ እድሪኮ የሲዊዝ ተወላጅ ከጋምቤላ ከጠረፍ አካባቢዎች ሽጎሌዎች መርጠው በማስመጣት በ1922 ዓ.ም የዘመናዊ የሙዚቃ ክፍል አቋቁመው በ1923 ዓ.ም በቀድሞው ንጉስ ቀ/ኃ/ሥላሴ የዘውድ በዓል ሰልፍ ላይ ተካፋይ ለመሆን በቅተዋል ።

በመቀጠልም በሙሴ አድረኮ አማካይነት በምት በልዩ ልዩ የትንፋሽ መሳሪያዎች በሰለጠኑ ወጣቶች በተፈሪ መኮንንና በዳግማዊ ምኒሊክ ት/ቤት ጥበቡ መታየት ጀመረ። ለስካውቶኣል የማርችንግ ባንድ ይቀርብ ነበር ።

በ1927ዓ.ም በሀገራችን የፋሽሽት ወረራ ባንዣበበት ወቅትም የኢትዮጵያ የሀገር ፍቅር ማህበር በሚል መጠሪያ በአቶ መኮንን ሀ/ወልድ መስራችነት የጠላት ወረራን ባንድ ልብና በወኔ ተነሳስቶ ድል ለመምታት እንዲቻል ታዋቂ ድምፅ መልካም ሽላዮች፣ ፎካሪዎች፣ የሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋቾችንና የጭፈራ ተሰጥኦ ያላቸውን ባሙያዎችን መርጦ በማሰባሰብ በዳግማዊ ሚኒሊክ አደባባይ ለህዝብ ትርኢት ቀርቧል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መሰንቆ ክራር፣ ዋሽንት፣ከበሮ የመሳሰሉት በስፋት መሰራት ጀመሩ።

ከጠላት ወረራ በኃላም በ1934ዓ.ም የሀገር ፍቅር ማህበር አባላት እንደገና በመጠናከር በሀገረሰብ የሙዚቃ መሳሪያዎች በመታጀብ ለህዝብ ማቅረቡን በስፋት ተያያዘ። የሬድዮ ፕሮግራም በተጀመረበት ወቅት በጣቢያው በመገኘት ሙዚቃቸውን ለአድማጭ ያቀረቡ ነበር። በ1938ዓ.ም ጀምሮ ሌሎች ክፍለ ሃገራት በመዘዋወር ትርኢታቸውን ያቀርቡ ነበር።

ከጠላት ወረራ በፊት ተቋቁሞ የነበረው የክቡር ዘበኛ ኦርኬስትራም በ1934ዓ.ም ተጠናክሮ በመቀቋቋም ጀምሮት የነበረውን ዘመናዊ ሙዚቀ እንቅስቃሴውን በማጠናከር 50ኛው ዓመት መጀመሪያ ላይ ደረሰ። በዚህ መካከል የምድር ጦር የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የሙዚቃ ቡድኖች ተቋቁመው በርካታ ስራዎችን ሰርተዋል ።

በ1937 ዓ.ም አለም አቀፋዊ የሙዚቃ ትምህርት ደንብና ሰርዓት በተከተለ መልክ በፕሮፌሰር አሌክሳንደር ኮንታሪቦች የፖላንድ ተወካይነት በሶስት መምህራን በቅድስት ስላሴ ካቴድራል አጠገብ በምትገኝ አነስተኛ ቤት ውስጥ የሙዚቃ ትምህርት መስጠት ተጀመረ። ከዚያ በኊላ የአለም አቀፋዊ ትምህርት በነጆርጅ በርድ በነሙሴ ነርሲስ ናልባንዲን መሪነት አስተባባሪነት የሙዚቃ ጥበብ እየታወቀና የዜማ ደራሲዎችም ብቅ ብቅ ማለት ችለዋል። በ1940 ዓ.ም አካባቢ በብሔራዊ ቲያትር ቤት ዘመናዊ ሙዚቃ ከመጀመሩ በፊት በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት በነበረው ቲያትርና ሙዚቃ ማስፋፊያ ክፍል

ወጣት የሙዚቃ ባለሙያዎች በመሰባሰብና በማሰልጠን የትንፋሽ ባንድ በመባል ታውቀው ነበር ፡፡

በመቀጠል በ1948 ዓ.ም የቀድሞው ቀ/ኃ/ሥ የአሁኑ ብሔራዊ ትያትር ቤት 25ኛው የዘውድ በዓል በማስመልከት የዘመናዊ ኦርኬስትራ በርታ ዜማዎች በድምፅና በሬድዮ ለህዝብ አበርክቷል፡፡ በዚሁ ቲያትር ቤት በ1950ዓ.ም የሀገረሰብ ሙዚቃ ቡድን ተቀነባብሮ ለመድረክ በቅቷል፡፡

ከ1951 ዓ.ም በኃላ የፖሊስ ሰራዊት የረቂቅ ሙዚቃ /የሲንፎኒ ኦርኬስትራ/ በማሰልጠን ብቻ የውጭ ሀገር ዜጎች ከፍተኛ የሆነ አስተዋፅኦ አበርክተዋል በ1955 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ኦርኬስትራ የሀገረሰብ ሙዚቃ መሳሪያዎችና የተለያዩ ብሄረሰቦችን አሰባስቦ ብሄራዊ መልክ ለመስጠት ተቋቁሟል፡፡

በ1959ዓ.ም በዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ ውስጥ አሸናፊ ከበደ ዳይሬክተርነት ተቋቁሞ የነበረው የብሔራዊ ሙዚቃ ትምህርት ቤት የአለም አቀፋዊ የሙዚቃ ጥበብ ስፋ ባለ መልክ ለማስፋፋት በ1960 ዓ.ም የቡልጋሪያ መንግስት ወደ አስመራ ህንፃ በማዛወር በ1962ዓ.ም በታላቁ ኢትዮጵያ የሙዚቃ በቅዱስ ያሬድ ስም በመያዝ ተመርቆ ተከፈተ፡፡ ትምህርት ቤቱም መደበኛውን የሙዚቃ ትምህርትና የዓለም አቀፍ መሳሪያዎችን በማካተት ስራውን ማካሄድ ቀጠለ፡፡

ከጠላት ወረራ በፊት በተወሰነ ትምህርት ቤቶች ይሰጥ የነበረው የሙዚቃ ትምህርትም በሌሎች ክፍላተ ሀገር በደሴ፣ በአሰላ፣ በሐረር፣በናዝሬት እስከ 1960 ዓ.ም አጋማሽ ድረስ ቀጥሎ ነበር ፡፡

የዘመናዊ ሙዚቃ እድገት በክበባትና በሆቴሎች ከተቋቋሙት የመዝናኛ የሙዚቃ ባንዶች /ቡድኖች/ በተለይ እስከ 1940ዎቹ ድረስ ባለው ወቅት በመጠንም ሆነ በዓይነታቸው ከጊዜ ወደ ግዜ እየተበራከቱ መጥተዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜም የዘመናዊ ሙዚቃ ይዘት ምንም እንኳን እያደገ ቢመጣም ከአለም እድገት አኳያ ስንመለከተው እንደተፈላጊነቱ የእድገት ደረጃው ሊጨምር አልቻለም ፡፡

**ታላላቅ አገር አቀፍ የሙዚቃ ደራሲያን ታሪክና ስራቸው**

**አሸናፊ ከበደ**

አሸናፊ ከበደ በ1930ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደ፡፡ እሱም ገና በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ት/ቤት ይማር በነበረበት ጊዜና በሐረር መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም ሙዚቃ በሚማርበት ወቅት የሙዚቃ ስሜት እንዳለው ያሳይ ነበር፡፡ ከሀረር መምህራን ማሰልጠኛ እንደተመረቀ በቀዳማዊ ኃ/ስላሴ ዮኒቨርስቲና በወጣቶች ክርስቲያናዊ ማህበር /YMCA/ ውስጥ ሙዚቃ ያስተምር ነበር ፡፡

ከዚያም ኢስትማን ስኩል ሙዚክ (Eastman School music) ፎችስታሪ በተባለው ዩኒቨርስቲ ሙዚቃ በመማር የመጀመሪያ ዲግሪውን አግኝቷል፡፡ በ1954 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ በመመለስና የሙዚቃ ትምህርት ቤትን በመክፈት የት/ቤቱ ዳይሬክተር ሆነ ፡፡ ወደ አሜሪካ ከመመለሱ በፊት የተለያዩ ሙዚቃዎችን ሊደርስ ችሏል፡፡ የያሬድ የሙዚቃ ት/ቤት ርዕስ መምህር በሆነበት ወቅት የ25 ዓመት ወጣት እንደነበር የሚታወቅነው ፡፡ የኢትዮጵያን ሙዚቃ ለአለም ህብረተሰብ ለማስተዋወቅ ከፍተኛ ጉጉት ነበረው ፡፡

በመሆኑም በወቅቱ የትምህርትና ስነ ጥበብ ሚኒስቴር የነበሩትን አቶ አካል ወርቅ ሀብተወልድን ባህላዊ የሙዚቃ ባለሙያዎችን አሰባስቦ በአውሮፕላን ወደ ኢስያ እንዲሄዱ ቢጠይቃቸው አላማው ስለአለገባቸው በጊዜው ተቃውመውት ነበር ፡፡

ይሁን እንጂ ራሱ ኃላፊነት በመውሰድ ሙዚቀኞቹን ይዞ ሊሄድ ሲነሳ ሚኒስተሩም ዓላማው ስለገባቸው በቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ተገኝተው በመሸኘት የማስታወሻ ፎቶግራፍ አብረው ተነስተዋል፡፡

በስራው ተደናቂነት ስላገኘ ቀ/ኃ/ሥላሴ በቀ/ኃ/ሥላሴ ቲያትር ቤት ገብተው በማየት ሽልማት አድርገውለታል፡፡ ባለዋሽንቱ እረኛ የተባለውን የመጀመሪያውን የሙዚቃ አልበም ሲያሳትም ከንጉሱ እጅ የገንዘብ ሽልማት አግኝቷል፡፡

በ1959ዓ.ም ብሔራዊ የሙዚቃ ደራሲ በመባል የቀ/ኃ/ስላሴን ልዩ ሽልማት አግኝቷል፡፡ በያሬድ የሙዚቃ ት/ቤት በርዕሰ መምህርነት ጥቂት ወራት እንደሰራ ወደ አሜሪካ በመመለስ የሁለተኛና የዶክትሬት ዲግሪውን እስከ 1964ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ሙዚቃ ላይ ፅፏል፡፡

በ1962 ዓ.ም በረዳት ፕሮፌሰርነት በኢትዮ ሙዚቃ ኮሌጅ ፕሮግራም ዳይሬክተርነት በኲዊንስ ኮሌጅና በሲቲ ዩኒቨርስቲ ኦፍ ኒወርክ የሰራ ሲሆን አሸናፊ ከበደ ደራሲ ከመሆን አልፎ በጥሩ አስተማሪነትም የታወቀ ኢትዮጵያዊ አርቲስት ነው፡፡

**ፀጋዬ ደባልቄ**

ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው የሙዚቃ ደራሲያን አንዱ አቶ ፀጋዬ ደባልቄ ነው፡፡ ይህ ሙዚቀኛ በያሬድ ሙዚቃ ት/ትቤ የሙዚቃ ትምህርት በመስጠት በብሄራዊ ቲያትር የሙዚቃ ስራዎችን የሙዚቃ ድርሰት በመድረስና በመሳሰሉት ለሙዚቃ እድገት ጥረት ያደረገ ሰው ነበር ፡፡ በተለይም በማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ የሙዚቃን ላይብረሪ በመመስረት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

ከሰራቸው ስራ ውስጥ ተወዳጅነት ያገኘው የሙዚቃ ድርሰት ጎፈሬ ጎፈሬ የተባለው ነው፡፡ ድርሰቱን ለክር መሳሪያዎችና የተለያዩ ድርሰቶቹ ለተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎች የሰጠ ሲሆን ብዙዎቹ ድርሰቶቹ የተደረሱት ባህላዊ ዜማዎችን መሰረት በማድረግ ነው ፡፡

**ነርሲስ ናልቫንድያን**

በኢትዮጵያ ለዘመናዊ ሙዚቃ መሰረት የጣሉት አርመናዊው ኢትዮጵያዊ ነርሲስ ናልቫንድያ እንደነበሩ በኢትዮጵያ የዘመናዊ የሙዚቃ ታሪክ ያወሳል ኢትዮጵያዊው ቫዮሊኒስትና የሙዚቃ ደራሲ ነርሲስ ናልቫንዲየን በህብረ ድምፅ /በኳየር/በቫዬሊን/ በክር መሳሪያ/ የቀድሞ ተማሪዎችን በማሰልጠን ከዚያም ከ1954-1957 ዓ.ም ስድስት ኪሎ ዩኒቨርስቲ ግቢ በሳቸው መሪነት ብሔራዊ የሙዚቃ ት/ቤት ተብሎ በተሰየመው ቦታ የሙዚቃ ትምህርት በመስጠት ያገለገሉ ሰው ናቸው፡፡

እሳቸውም በ1962 ዓ.ም በኢትዮጵያ ቤተክህነት በሙዚቃ ደራሲነት በታወቁ በቅዱስ ያሬድ ስም በተከፈተው ት/ቤት ነረሲስ ናልባዲያን በመደበኛ የኳየር/ የህብረ ድምፅ/ መምህር በመሆን አገልግለዋል፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ግቢ ክበብ ናዝሬት ት/ቤት አድማጭን በሚማርክ የህብረት መዝሙሮችን ሰርተዋል፡፡ ከሰራቸውም ጥቂቶቹ ፅጌረዳ፣ አፍሪካ የሺ ሀረጊቱና እንኮይ ናት ያባይ ዳር ወዘተ...የመሳሰሉት ድንቅ ስራዎች ይገኙበታል፡፡ ምንም እንኳን እሳቸው በአሁን ጊዜ በህይወት ባይኖሩም ስራቸው ህያው ሆኖ ይኖራል፡፡

## የውጭ ሀገር የሙዚቃ ታሪክ

በህብረተሰብ የእድገት ታሪክ ውስጥ ለዘመናዊ ሙዚቃ ድርሰት መሰረት ሊሆኑ የቻሉ የብዙ መቶ አመታት ጥናትን ምረምሮች በተለያዩ ሀገሮች ውስጥ በሚገኙ የሙዚቃ ባለሙያዎች ሲካሄዱ ቆይተው ጊዜ የፈተናቸው አስተማማኝ የአሰራር ስልቶች አሁን ለምንገለገልበት የሙዚቃ ድምፅ አቀራረፅ ደንብ ሙሉ ተቀባይነት አግኝተው የዳበሩት ከአስራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

ከዚህ ወቅት ጀምሮ የሙዚቃ ታሪክ የራሱ የሆነ ክፍለ ዘመን ማለትም የአደራረስ ባህርይ መለያ ኖሮት በግል ወደሚመራበት ደረጃ ተሸጋግሮል፡፡እነዚህም የሙዚቃ ክፍለ ዘመናት የሚከተሉት ናቸው

1. የባሮክ ሙዚቃ ክፍለ ዘመን   ከ 1600 ---- 1750
2. የክላሲክስ ሙዚቃ ክፍለ ዘመን  ከ ከ1730 — 1820
3. የሮማንቲክ ሙዚቃ ክፍለ ዘመን ከ 1815 --- 1910

ሞደርን የሙዚቃ ክፍለ ዘመን ከ 1900 ጀምሮ ሲሆን ከዚህ በመቀጠልም በዘመኑ የነበሩትን ዓለም ዓቀፍ ታዋቂ የሙዚቃ  ደራስያንን እንተዋወቃለን፡፡

**ታላላቅ ዓለም አቀፋዊ የሙዚቃ  ደራሲያን  ታሪክና  ስራዎቻቸው**



**ዮሀንስብሀትያን ባህ 1685 -- 1750**

ዮሀንስብሀትያን ባህ በባሮክ ክፍለ ዘመን ኢሰናች በምትባል የጀርመን ከተማ በ1685ዓ.ም ተወለደ ፡፡ ባህ እስከ 18 ዓመት እድሜው ድረስ በትምህርት  ላይ ቆይቶ በ18 ዓመት እድሜው አርንስታድ በምትባል ቤተክህነት  ውስጥ በኦርጋን ተጫዋችነት  ስራ ጀመረ፡፡

ባህ በአለም ላይ ተወዳጅነትን ያተረፈው በፖሊፎኒ የሙዚቃ ስራ በማስፋፋት ሲሆን በተለይ በኦርጋን ለፒያኖ ለተለያዮ ለአለም አቀፍ የሙዚቃ መሳሪያዎች ድርሰቶቹን በሶናታ መልክ በመሳሰሉት አቅርቧል፡፡



**ሞዛርት** (W.G.A Mozart) 1756-1791

ሞዛርት በኦስትሪያ ሳልዝበርግ በምትባል ከተማ ተወለደ፡፡ የሞዛርት አያት በጣም የታወቀ የቫዮሊን ተጫዋቾችና የሙዚቃ ደራሲ ነበር፡፡ ወደ ሞዛርት አባት ቤት ብዙ የሙዚቃ ባለሙያዎች ይመጡ ነበር፡፡ ስለዚህ ሞዛርት በህፃንነቱ የተለያዩ ቃና ያላቸው ሙዚቃ በመስማት ስሜቱ ወደ ሙዚቃ ሊሳብ ቻለ፡፡ የሞዛርት ታላቅ እህትም የሙዚቃ ችሎታ ስለነበራት በስምንት አመቷ ፒያኖ ለመምታት ችላለች ፡፡ በዚህም ሞዛርት በ2 ና በ3 ዓመቱ የሙዚቃ ፍቅር አደረበት ፡፡ ሞዛርትም አባቱን ፒያኖ ለመምታት በሚለምነው ወቅት ትንሿ አፍንጫህ የፒያኖውን ኪቦርድ ስትነካ ትጫወታለህ እያለ ይቀልድ ነበር ፡፡ ሞዛርት ግን እስቲያድግ ድረስ ለመቆየት አላስቻለውም፡፡ ዘወትር ወደ ፒያኖ ዘንድ በመሄድ እየተፍጨረጨረ የፒያኖውን ቃታ ይነካካ ነበር ፡፡

አንድ ቀን ህፃኑ ሞዛርት አባቱን ፒያኖ ለመምታት ችያለሁና ስማ ብሎ ከወንበር ላይ በመቆም አንድ አይነት ሙዚቃ በፒያኖ አሰማው ፡፡ በዚህ ጊዜ አራት አመት እንኳን አልሞላውም ነበር ፡፡ አባቱና ቤተሰቦቹ በጣም ተገረሙ፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አባቱ የሙዚቃ ትምህርት ይሰጠው ጀመር፡፡ ሞዛርት የሙዚቃ ልምምድ በሚያደርግበት ጊዜ ፈፅሞ ሰው አያነጋግርም ፡፡ ለሙዚቃ ብቻ በጣም ፍቅር ነበረው፡፡ ሞዛርት አባት ቤት ከሚሰባሰቡት የሙዚቃ ባለሙያዎች አንዱ ቫዮሊን ተጫዋች የአባቱ ጓደኛ ነበር

፡፡ ሞዛርትም በዚህ ሰው ቫዮሊን አጨዋወት በጣም ይደሰት ነበርና ቫዮሊን ለመጫወት የጋለ ፍላጎት አደረበት ፡፡ አስተማሪው ቫዮሊን ለመጫወት ቻለ፡፡

አንድ ቀን ያባቱን ቫዮሊን እንዲጫወትበት ቢጠይቀው አባትየው አይችልም በማለት ከለከለው፡፡ ሞዛርት በመከልከሉ ስላለቀሰ የአባቱ ጓደኛ ቫዮሊን እንዲጫወት ፈቀደለት፡፡ ሞዛርትም ከጥቂት ሰዓት በኃላ በቫዮሊን አመታት ትንግርት የሆነ ሙዚቃ ተጫወተ ፡፡ ሰው ሁሉ በጣም ተገረመ፡፡ ህፃኑ ሞዛርት በሚያደርገው ተአምር ወላጆቹም ተደነቁ አባቱም በይበልጥ መከታተልና ማስተማሩን ቀጠለ፡፡ ከጥቂት ወራት በኃላ ሞዛርት ልዩ ልዩ ሙዚቃ መጫወት ቻለ፡፡

ሞዛርት ከ1763-1766 ማለትም ከ7-10ዓመት እድሜው ባለ ግዜ ውስጥ የሙዚቃ ድርሰት ጀምሮ ነበር፡፡ በህይወት ቆይታው ጊዜው 21 ለፒያኖ ኮንሰርት የሚሆኑ የሙዚቃ ድርሰት፣ 1 ክራርኔት እንዲሁም የተለያዩ ብዙ ድርሰቶች የጻፈ ታዋቂ የሙዚቃ ደራሲ ነበር፡፡ አሁንም ድርሰቶቹ በስራ ላይ እየዋሉ ሲሆን ወደ ፊትም በስራ ላይ ይውላሉ፡፡



**ሉድ ዊንግ ባን ቬትሆቨር 1770 - 1828**

ቬትቬን የኖረው ከ1770-1827 ዓ.ም በክላሲካል ዘመን ሲሆን የተወለደው ሀገር ቦን በምትባል ከተማ ነው ፡፡ ቤቶቨን ገና በ 11 አመት አድሜው ቦን ውስጥ የህብረ ድምፅ የፒያኖ ረዳት ተጫዋች በመሆን ተቀጠረ፡፡ በ 18 ዓመቱም ቦን በሚገኘው የኒቨርሰስቲ በመግባት የፍሎሶፊ ትምህርትን ተከታትሏል፡፡

በወጣትነት ዘመኑ በፒያኖ የአጨዋወት ዘዴው በጣም ጥበብ የተሞላበት ስለነበር በአድማጩ ዘንድ እጅግ አድናቆት ነበረው፡፡እሱም የድርሰት ስራውን ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍ እያደረገ በመሄዱ

ESD

ብዙ የሙዚቃ ድርሰቶች ፅፎል፡፡ ከነዚህም ውስጥ 9 ትልልቅ ሲንፎኒዎች፣1 ኦፔራ፣32 የፒያኖ ሶናታዎች እንዲሁም ለተለያዩ ዓለም ዓቀፍ የሙዚቃ መሳርያዎች የተለያዩ ድረሰቶች ፅፏል፡፡ ቤቶቨን የጆሮ ህመም ቢያጋጥመውም ድርሰቱን ከመፃፍ አልተቆጠበም ነበር፡፡

ቤቶቨን ደራሲ፣ፒያኒስት በተጨማሪም ኮንንዳክተርም ነበር፡፡

**ማነቃቅያ የክለሳ ጥያቄዎች**

1. የቅዱስ ያሬድ የድምፅ መመርያ ምልክቶች ስንት ናቸው
2. በተማራችሁት መሰረት ለኢትዮጵያ ሙዚቃ እድገት አስተዋፅኦ ካደረጉ ታወቂ የሙዚቃ ሰዎች ሁለቱን ጥቃሱ
3. ከውጭ ሀገር ታላላቅ የሙዚቃ ደራስያን ሁለት ጥቀሱ

# ምዕራፍ 4

## የሙዚቃ መሳርያዎች

ዓላማ

- ✓ የሀገራችንን የሙዚቃ መሳርያዎች ይተዋወቃሉ
- ✓ የሙዚቃ መሳርያዎችን ክፍፍል ይረዳሉ
- ✓ የቅድመ መደበኛ ሙዚቃ መሳርያዎችን ይተዋወቃሉ

**የሙዚቃ መሳርያዎች**

**የአዮጵያ ባህላዊ የሙዚቃ መሳርያዎች ትውውቅ**

ኢትዮጵያ የብዙ ብሄር ብሄረሰቦች ሀገር እንደመሆኗ መጠን ልዩ ልዩ ባህላዊ የሙዚቃ መሳርያዎች አሉት፡፡ አነዚህም ባህላዊ የሙዚቃ መሳርያዎች በ 3 ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ፡፡

እነዚህም የሙዚቃ መሳርያዎች --

1. የክር ወይም የንዝረት
2. የትንፋሽ
3. የምት ሙዚቃ መሳርያዎች በመባል ይታወቃሉ፡፡

1. የክር ወይም የንዝረት ሙዚቃ መሳርያ የሚባሉት
    - ክራር
    - በገና
    - መሰንቆ
    - ዲታ ወዘተ…
2. የትንፋሽ ሙዚቃ መሳርያ የምንላቸው
    - ዋሽንት

- እምቢልታ
- መለከት
- ፋነፋ
- ጡሩንባ ወዘተ…

3. የምት ሙዚቃ መሳርያዎች የምንላቸው

- ከበሮ
- አታሞ
- ነጋሪት
- ከረቤ
- ቅል ወዘተ…

ከነዚህ ባህላዊ የሙዚቃ መሳርያዎቻችን መካከል ለማንኛውም ብሄር ብሄረሰብ ዜማ አጨዋወት ተስማሚ የሆኑና እስከ አምስት ድምጽ ለማውጣት የሚችሉ መሳርያዎች አሉ፡፡እነዚህ ለዜማ፤ለመዘመር፤ለዘፈን አጨዋወት ተስማሚ የሆኑትና እስከ አሁን የታወቁት የባህል መዚቃ መሳርያዎቻችን የሚከተሉት ናቸው

- መስንቆ
- ዋሽንት
- ክራር
- በገና
- ቶም የሚባሉትን ያካትታል፡፡

ከንፈርን በማጥበቅና በማላላት በትንፋሽ ሀይል ሁለትና ሶስት ድምፅ ብቻ የሚያወጡ ድምፀ ውስን የሙዚቃ መሳርያዎችም አሉ፡፡ እነሡም

- እምቢልታ
- መለከት የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## የቅድመ መደበኛትምህርት የሙዚቃ መርጃያ መሳርያዎች



በአካባቢ በሚገኙ ቁሳቁሶች በመጠቀም ለህጻናት የሚያገለግሉ የሙዚቃ መሳርያዎችን ቀላል የአሰራርና የአጠቃቀም ዘዴ ከዚህ በመቀጠል ተዘርዝረዋል፡፡

1. የምት ዱላ (Rhythm stick)

1.1 አስፈላጊ ነገሮች -- ድብልብል እንጨቶች ባለ 2 ሳ.ሜ ውፍረት፡ የብርጭቆ ወረቀት፡ ቨርኒሽ

1.2 አሰራር፡-

- ባለ ሁለት ሳ.ሜ ውፍረት ያለውን ድቡልቡል እንጨት በ 18 ሳ፣ሜ ርዝመት መቁረጥ፡፡ ይህ ባለ አጭር የምት ዱላ ነው፡፡
- ባለ ሁለት ሳ.ሜ ውፍረት ያለውን ድቡልቡል እንጨት በ30 ሳ.ሜ ርዝመት መቁረጥ፡፡ ይህ ለረጅም የምት ዱላ ነው፡፡

1.3 አጠቃቀም የምት ዱላዎችን በማጋጨት የሚፈለገውን ድምፅ ማግኘት ይቻላል፡፡

2. የማጨብጨብያ ጣውላ

2.1 አስፈላጊ ነገሮች ጠፍጣፋ ጣውላ ውፍረት 2 ሳ.ሜ ፤ብርጭቆ ወረቀት፤ሚስማር ባለ 3 ሳ.ሜ፤ ቨርኒሽ፤ኮላ

2.2 አሰራር፡-

12 x 8 አድርጎ ጣውላውን መቁረጥ፤መሀል ለመሀል ለመያዥያ የሚሆን ድቡልቡል ዋናው ጣውላ መሀል ላይ ፈልፍሎ በኮላ አያይዞ ማስገባትና እንዲጠናከርም በምስማር መምታት፤በብርጭቆ ወረቀት አለስልሶ ቨርኒሽ መቀባት፡፡

2.3 ሁለቱ የጣውላ እንጨቶችን በማጋጨት ድምፅ መፍጠርይቻላል፡፡

3. ፅናፅል

3.1 አስፈላጊ ነገሮች ቆርኪዎች፤ወፈር ያለ ሽቦ፤ባለ 2 ሳሜ ውፍረት ያለው እንጨት፤የብርጭቆ ወረቀት፤ቨርኒሽ

3.2 አሰራር


- ✓ ባለ ሁለት ሳ፣ሜ ውፍረት ያለውን እንጨት በ16 ሳ፣ሜ ርዝመት መቁረጥ
- ✓ ከጫፍና ከጫፍ 1ሳ.ሜ ገባ ብሎ ዙርያውን መከርከር
- ✓ ቆርኪዎቹን መሀላቸውን በሚስማር ከበሱ በሆላ ሽቦ ውስጥ ማስገባት የቆርኪዎቹ ብዛት ከ10 -15 ሊሆን ይችላል

የተከረከረመው ቦታ ሽቦውን ጥብቅ አድረጎ ማሰር ይህ የሚጠቅመው ሽቦው ከድቡልቡሉ እንጨት እንዳይወጣ ነው፡፡

ከዚህ በላይ ከተጠቀሰውም ሌላ ባላ ፅናፅል መስራት ይቻላል፡፡አሰራሩም ከላይ የተጠቀሰውን አንዳንድ መሰረተ ሀሳቦችን በመጠቀም ይሆናል፡፡

3.3 አጠቃቀም ኪሽ ኪሽ የሚል ድምፅ እንዲሰጥ ማንከሻከሽ

4. ትርያንግል




4.1 አስፈላጊ ነገሮች ግማሽ ሳ.ሜ ውፍረትና 48 ሳ.ሜ ርዝመት ያለው ድቡልቡል ብረት፤ጠንካራ ክር ባለ 12 ሳ.ሜ፡፡

4.2 አሰራር፡-

ባለ 48 ሳ.ሜ ድቡልቡሉን ብረት በ 18 ሳ.ሜ ርቀት ልዩነት በመለካት ጫፍና ጫፎቹ እስኪቀራረቡ ድረስ በትሪያንግል ቅርፅ ዓይነት ማጉበጥ ትሪያንግሉን ለማንጠልጠል አንደኛው አንግል ጋር በክር ማንጠልጠል፡፡ለትሪያነግሉ መምቻ የሚሆነውን የወፍራም ምስማር ሹል ጫፍ ማዶለዶም፡፡

4.3 አጠቃቀም ትሪያንግሉን በክር አንጠልጥሎ በምምቻው መምታት በዚህ ጊዜ ቅጭልቅጭል የሚል ድምፅ ይሰጣል፡

## 5. አነስተኛ ከበሮ



5.1 አስፈላጊ ነገሮች ባለ አንድ ጋሎን የቀለም ቆርቆሮ ወይም ተመሳሳይ ነገር፤የለፋ የፍየል ቆዳ፤ገመድ፤ሽቦ ወይም ጠፍር

5.2 አሰራር፡-

- ቆዳው እንዲርስ ለሁለት ቀን ያህል በውሃ መዘፍዘፍ
- የጋሎኑን የላይና የታች ክፍል ነቅሎ ማውጣት
- ቆዳው ከራሰ በኋላ በቆርቆሮው ላ ወይም ታች ክብ ልክ አስፍሮ ቆዳውን መቁረጥ
- የቆዳውን ዳርና ዳር ትርፍ ቦታ ዙርያውን በመብሳት ይህ የሚረዳው ገመድ ጠፍሩ ወይም ሽቦው ከሌላው ቆዳ ጋር እንዲሳሳብና እነዲወጠር ነው
- ቆዳውን በክቡ ዙርያ አድርጎ ሥሩንና ሌሎቹን የሚያያይዙትን እያቆላለፉ ማሰር፡፡በዚህ አየነት ሁኔታ ጥሩ ከበሮ መስራት ይቻላል፡፡

5.3 አጠቃቀም በእጅ ወይንም በከበሮ መምቻ ከበሮውን መምታት ቡምቡም የሚል ድምፅ ይፈጥራል፡፡

***የማነቃቂያ ክለሳ ጥያቄዎች***

1. የሙዚቃ መሳርያዎች በስንት ይከፈላሉ አይነታቸውን ጭምር ጥቀሱ፤
2. በትንፋሽ አማከኝነት ድምፅ ከሚሰጡት የሙዚቃ መሳርያዎች ሶስቱን ጥቀሱ
3. ራሳቸውን ችለው ለብቻቸው ዜማ መጫወት ከሚችሉ የሀገራችን የባህል ሙዚቃ መሳርያዎች ሁለት ጥቀሱ
4. የቅድመ መደበኛ የሙዚቃ መርጃ መሳርያዎችን ስም ዘርዝሩ

# ምዕራፍ 5

## የኢትዮጵያ ሙዚቃ ዜማዎችና ቅኝቶች

**ዓላማ ፡-**

- ✓ ስለ ኢትዮጵያ ሙዚቃ ዜማና ቅኝት አመሰራረት ይረዳሉ
- ✓ የኢትዮጵያ ሙዚቃ የተመሰረተበትን ድመፅ አጠቃቀም ይተዋወቃሉ

የኢትየጵ ሙዚቃ ዜማዎችና ቅኝቶች

የተለያዩ ሀገሮች ሙዚቃቸው የሚመሰረትበትን መሰረታዊ ቃናዎች የተለየ ስያሜዎች ይሰጧቸዋል፡፡ከነዚህም ውስጥ ለምሳሌ የህንዱ ራጋ፤የዩጋንዳው ሚክ፤የአረቦች ማካም በመባል ቅኝትን መሰረታዊ የሙዚቃ ቃናዎችን ለመግለፅ ይጠቀሙበታል፡፡ለቅኝት የተለያዩ ትርጉሞች ሊሰጡት ይስተዋላል፡፡ለምሳሌ የሙዚቃ ደራሲና ተመራማሪው አሸናፊ ከበደ ቅኝትን ከአለማዊ ሙዚቃ መሳርያዎች አቀኛኘት ስርአትና ከዜማዎች የቃና አወቃቀር አንጻር ትርጉሙን ይሰጣል፡፡ከዚህ አንጻር ቅኝት ሙዚቃዎች የሚመሰረቱበትና መሰረታዊ የቃና (ፒች) ስብስብ ነው፡፡

ፔንታቶኒዚም በተለያዩየሙዚቃ ስርአት ውስጥ ለምሳሌ በቻይና፤በስኮትላንድ፤በጃፓን፤በኢትዮጵያና በህንድ ይገኛል፡፡ፔንታቶኒክ ስኬል በመላው ዓለም በተለያየ ፎርም በጥንታዊና ባህላዊ ሙዚቃ ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡በመሰረቱ ፔንታቶኒክ በመሰረታዊ የአምስት ድመጽ ዜማ ላይ የተዋቀረ ነው፡፡

ከዚህ በመነሳት ቅኝት ማለት አንድ መሰረታዊ የሆነ የድምፅ ፎርሙላ ሲሆን በዚህ መሰረታዊ የድምፅ ፎርም ውስጥ የተለያዩ ዜማዎች ሊዜሙና ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡

ቅኝት ከዘመኑ አጠቃቀም እስኬል ከሚለው ጋር ይመሳሰላል፡፡እስኬል ማለት የድምፅ መውረጃና መሰላል ሲሆን የተለያዩ አይነት የስኬል አይነቶችም አሉ ፡፡

እነሱም ፡-

1. ክሮማቲክ አስኬል -- ባለ አስራሁለት ድምፅ መሰላል
2. ዲያቶኒክ እስኬል -- ባለ ሰባት ድምፅ መሰላል
3. ፔንታቶኒክ እስኬል -- ባለ አምስት ድምፅ እስኬል

የኢትዮጵያ ሙዚቃ የዜማ ምስረታ ፔንታቶኒክ እስኬል በተባለው በባለ አምስት ድምፅ ላይ በመመስረት አራት የዜማ መመስረቻ ቅኝቶች አሉት፡፡

እነሡም

1. ትዝታ ቅኝት
2. ባቲ ቅኝት
3. አንቺሆዬ ቅኝት
4. አምባሰል ቅኝት ኛቸው፡፡

**የማነቃቅያ ክለሳ ጥያቄዎች**

1. የኢትዮጵያ ሙዚቃ የተመሰረተው በባለ ስንት ድምፅ ላይ ነው?
2. የኢትዮጵያ የዜማ ቅኝቶች ስንት ናቸው ስማቸውን ጭምር ጥቀሱ፤

# ምዕራፍ 6

## ሶልፌጆ

**ዓላማ፡-**

- ✓ የሶልፌጆን ምንነትና ትርጉም ይረዳሉ፤
- ✓ መሰረታዊና ቀላል ምቶችን ይተዋወቃሉ፤

**ሶልፌጆ (solfeggio)**

ሶልፌጆ የሚለው ቃል የተገኘው ከፈረንሳይ ቋንቋ ሲሆን ትርጉሙም የሙዚቃ ድምፆችና የምት ጥናት ማለት ነው፡፡

በሶልፌጆ የትምህርት ዘርፍ የድምፅ አወጣጥ የድምፅ አሰባበር እና የሙዚቃ ኖታዎችን በማየት ያለ ሙዚቃ መሳርያ በድምፅ ብቻ የመዘመር ዘዴዎች ይጠናሉ፡፡

በአጠቃላይ ሶልፌጆ ሙዚቃን በጆሮ አዳምጦ በኖታ የመጻፍ እንዲሁም በኖታ የተፃፈን ዜማ በድምፅ አስተካክሎ የመዘመር ጥበብ ነው፡፡

**መሰረታዊና ቀላል ኖታ አነባብ**

እያንዳነዱ ኖታ የራሱ የሆነ የጊዜ ቆይታና የአነባብ ስልት አለው፡፡በሙዚቃ ህግ አንድ ምት የምንለው በውስጥ እግራችን ከላይ ተነስተን ወለሉን ነክተን ስንመለስ ወይም የቀኝ እጃችን መዳፍ ከደረታችን ትይዩ በመነሳት የግራ እጃችን መዳፍን ነክቶ ሲመለስ እንደ አንድ ምት ይቆጠራል፡፡በዚህ መሰረት ኖታዎች ያላቸውን የጊዜ ቆይታ ዋጋ መሰረት በማድረግ ጀማሪዎች የኖታ ንባብን ልምምድ ያደርጋሉ፡፡


በዚህ መሰረት ቀጥሎ የሚታዩትን ኖታዎች የንባብ ልምምድ እናደርጋለን፡፡

**መሰረታዊ ምቶችን መተዋወቅ**

መሰረታዊ ምቶች የምንላቸው መገለጫቸው የርምጃ ምት፤የሩጫ ምት፤እንዲሁም የመንጠር ምትን ያካተተ ነው፡፡


1. የርምጃ ምት  የርምጃ ምት በኖታ ሲገለፅ ተደጋጋሚ እሩብ ኖታዎች ማንበብ ይሆናል

   ምሳሌ




2. የሩጫ ምት  የሩጫ ምት በኖታ ሲገለፅ ተደጋጋሚ ሁለት አንድ ስምንተኛ ኖታዎች ይሆናሉ።

ምሳሌ





የመንጠር ምት  የመንጠር ምት በኖታ ሲገለፅ አነድ ስምንተኛ የእረፍትና አንድ ስምንተኛ የእረፍት ኖታ በተደጋጋሚ ሲነበቡ የሆናል

**ምሳሌ፡-**



**በስታፍ ላይ መሰረታዊ የኖታዎች አፃፃፍ**







## በኖታ መዘመር

### የማነቃቂያ ክለሳ ጥቄዎች

1. የሶልፌጀን ምንነት አሰረዱ
2. በህፃናት አለም የሚዘወተሩትን መሰረታዊ ምቶችን ግለፁ

## ምዕራፍ 7

## ሙዚቃ ለህፃናት ያለው ጠቀሜታ

**ዓላማ፡-**

✓ በቅድመ መደበኛ ሙዚቃ ለህፃናት ያለውን ጠቀሜታ ይረዳሉ

**ሙዚቃ ለህፃናት ያለው ጠቀሜታ**

**ሙዚቃ ባደገባቸው ሀገሮች የሙዚቃ ትምህርት ከመደበኛ አጠቃላይ ትምህርት ጋር አብሮ መሰጠት የሚጀምረው ከአፀደ ህፃናት ጀምሮ ሲሆን በዚህ እድሜ ላይ ለሚገኙ ሕፃናት ሙዚቃን ለማስተዋወቅ የሚደረግ ዘዴ ብዙ አይነት ነው**

**ለምሳሌ* ሕፃኑ መናገር ሲጀምር በጣም አስፈላጊ የሆሑ በራሱ የመጀመርያ ወይም አፍ መፍቻ k3k ጋር ዝምድና ያላቹን ዜማዎች ሪትሞችና ድምፆች የማድመጥ ልምድ እንዲያድርበት ይደረጋል የህፃኑ የእውቀት አድማስ እየ ሰፋ በሄደ ቀጥር አጠቃላይ የትምህርት እውቀቱ እንዲበለፅግ ለማድረግ ባህለዊ እንቅስቃሴዎችን በመጠቀም ቀላል መዝሙሮችን በአፍ መፍቻቸው እንዲዘምሩ ይደረጋል፡፡እነደዚሁም የባህላዊም ሆነ የዘመናዊ ሙዚቃ መሳርያዎችን በመተዋወቅ የሙዚቃ እውቀትን እንዲያዳብሩ ይደረጋል፡፡**

ከዚህ በመነሳትም ሙዚቃ ለህፃናት ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፤ ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል:

1.ሙዚቃን በራሱ እንደ አንድ ትምህርት ሲማሩት፥

- ✓ የተለያዩ ድምፆችን የማድመጥና የመለየት ክህሎትን ያዳብራሉ፤
- ✓ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ይተዋወቃሉ፤
- ✓ የቋንቋ ክህሎታቸውን ያዳብራል፤

2.ሙዚቃ ህፃናት በስነምግባር ታንፀው እንዲያድጉ ይረዳል

3 ሙዚቃ ለህፃናት ዐዕምሮ ዕድገት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል

4. መዝሙር ለህፃ ናት አካላዊ እድገት ከፍተኛ እገዛ አለው

4.1 መዝሙሩን በድምፃቸው በሚዘምሩበት ጊዜ

- ✓ ንግግራቸውን ያሻሽልላቸዋል
- ✓ ትንፋሽ አጠቃቀማቸውን ያሻሽልላቸዋል
- ✓ የሆድ የሳንባና የመተንፈሻአካላቶቻቸውን ያሰራል ጤናማም ያደርጋል

4.2 መዝሙሩ እንቅስቃሴ ሲታከልበት

- ✓ የሰውነት ቅርፃቸው የተስተካከለ እና ቀልጣፋ እንዲሆን ይረዳል
- ✓ የሰውነት ክፍሎቻቸው የህብረት እንቅስቃሰሴ የተቀናጀ እንዲሆን ይረዳል

በተጨማሪም የሙዚቃ እውቀትን የቀሰሙ ሕፃናት በሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ውጤታማ አንደሚሆኑና kንkን የመረዳት፤ የመናገር፤ የመፃፍ፤ሂሳብ የማስላት አካባቢያቸውን የመገንዘብ፤ወዘተ...የመሳሰሉትን የሚያበለፅጉባቸው መሆኑን በሙዚቃና በቴክኖለጂ ካደጉ ሀገሮች ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከሌሎች ትምህርቶችንም ለማስተማርያነት ያገለግላል

**የማነቃቅና የክለሳ ጥያቄ**

1. ሙዚቃ ለህፃናት የሚሰጠውን ዋናዋና ጠቀሜታዎችን ጥቀሱ

# ምዕራፍ 8

## የሙዚቃ ስሜት እድገት በህፃናተ ከልደት እስከ ስድስት አመት

ዓላማ፡-

- ✓ ሕፃናት ከልደት አስከ መደበኛ ትምህርት እድሜ ባላቸው የእድሜ ከልል በሙዚቃ ያላቸውን የስሜት እድገት ይረዳሉ ፤

<u>የሙዚቃ ስሜት እድገት በህፃናተ ከልደት እስከ ስድስት አመት</u>

- ✓ **ህፃን ልጅ ከተወለደ ከ10 እስከ 12-** ባሉት ቀናት ድምፅን ይሰማል ፡፡
- ✓ **በሁለተኛው ወር ላይ** _ለሚሰማው ድምፆች አንዳንድ ሁኔታዎችን ማሳየት ይጀምራል በተለይ ከ4- 5 ባሉት ወራት የተለያዩ ድምፆችን የመለየት አዝማሚያ ይታዩበታል።
- ✓ **ከመጀመሪያው አመት ጀምሮ** -_ህፃን ልጅ የሚሰማውን የሙዚቃ ድምፅ ባለበት ደረጃ በሚያወጣቸው ድም ፆች መልስ ለማስተላለፍ ይሞክራል።
- ✓ **በሁለተኛው አመት እድሜ**_ ሙዚቃን በሚሰማበት ጊዜ በሚሰማው የሙዚቃ ድምፅ የተለያየ ስሜቶችን ይገልፃል በብሩህ ፈገግታም ይንቀሳቀሳል፣ድምፅን በተመስጦ ያደምጣል፣ድምፅን የመለየት ችሎታውም ያድጋል፣የሚሰማውን የሙዚቃ ድምፅ ከጭብጨ ባ፣ከእግር እርግጫና ከሌሎችም እንቅስቃሴዎች ጋር እሪትምን ጠብቆ ለመንቀሳቀስ ይሞክራል።
- ✓ **በሶስተኛውና በአራተኛው አመት እድሜ**__**በህፃናት የመስማት ችሎታ ላይ የተለያየ የእድገት ልዩነት ሊታይ ይችላል**። ለምሳሌ_አንዳዶቹ የሰሙትን ሙዚቃ ዜማ (melody) ሰምተው በቀጥታ ማንፀባረቅ ሲችሉ አንዳንዶቹ ደግሞ ይህን ማድረግ ይከብዳቸዋል ። በዚህ እድሜ እራስን ችሎ የመዘመር ጥረት ሲያደርጉ ይታያል። በዚህ እድሜአቸው አጫጭር መዝሙሮችን አጥንተው በቀላሉ

የመዘመር ችሎታ ይኖራቸዋል ከመዝሙሩ ምት ጋር እንቅስቃሴን አክለው የመንቀሳቀስ ሁኔታ የታይባቸዋል።

- ✓ **አምስተኛው አመት እድሜ በህፃናት** ሁሉን የማወቅ ፍላጎት አይሎ የሚታይበት ጊዜ ነው ይህ ጊዜ ህፃናት ጥያቄዎችን በብዛት የሚያፈልቁበት ነው። በዚህ እድሜ ላይ አንድ ህፃን የደስታ የሀዘን ፣ ከፍና ዝቅ፣ቀስ ያለና ፈጠን ያለን ሙዚቃ ከመለየቱም በላይ የሙዚቃ ሪትምን ጠብቆ መንቀሳቀስ ፣መደነስ፣መጨፈር ይችላል።
- ✓ **ከ6_8 አመት ያለው እደድሜ_** ህፃናት ለመደበኛ ትምህርት ቤት የሚዘጋጁበት ጊዜ ነው።በዚህ ጊዜ የተለያዩ የሙዚቃ ድምፆችን የመለየት ድምፅን በመስማት የሙዚቃ መሳሪያውን መለየትና ከእንቅስቃሴ ጋር መዝሙሩን የማዛመድ ችሎታ ሊኖራቸው ይችላል።ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ጊዜ የሰሙትን የሙዚቃ ፀባይ የመናገር ችሎታ ይኖራቸዋል።

## ምዕራፍ 9

# የቅድመ መደበኛ የሙዚቃ ትምህርት ዓላማናይዘቶች

ዓላማ:-

- ✓ የቅድመ መደበኛን የሙዚቃ ትምህርት አላማና ይዘቶችን ይተዋወቃሉ ::
- ✓ የቅድመ መደበኛን የሙዚቃ ይዘቶችን የማስተማር ዘዴን ይተዋወቃሉ ::
- ✓ የቅድመ መደበኛን ናሙና መዝሙሮችን ይተዋወቃሉ ::

**የቅድመ መደበኛ የሙዚቃ ትምህርት ዓላማ**

1. ህፃናት ድምፅን ማድመጥና የመለየት ክህሎትን ያዳብራሉ፤
2. በየደረጃው የድምፅ ቆይታን ይገነዘባሉ፤
3. በመዝሙር አማካኝነት ከልዩልዩ ፅንሰ ሀሳቦች ጋር ይተዋወቃሉ፤
4. ከአካባቢያቸው ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ጋር ይተዋወቃሉ፤
5. አካላዊ እንቅስ ቃሴን ከሙዚቃው ሪትም ጋር የማዋሀድ ክህሎትን ያዳብራል ፤

**የቅድመ መደበኛ የሙዚቃ ትምህርት ይዘቶች**

የአፀደ ህፃናት የሙዚቃ ትምህርት ይዘቶች አራት ናቸው :: እነሱም:–

1 መዝሙር

2. ማድመጥ*

3.ሙዚቃዊ እንቅስቃሴ

4. የሙዚቃ መሳሪያዎች ትውውቅ ናቸው

1. **ማድመጥ ፡-**

**ዓላማ--** ህፃናት በአካባቢያቸው የሚሰሟቸውን ድምፆቸ የመተዋወቅና የመለየት ክህሎትን ያዳብሩበታል።

ከዚህ ቀጥሎ ህፃናት በማድመጥ ላይ የሚሰሯቸውን ሙከራዎች እናያለን ፡፡

**ምን ዓየነት ድምፅ ነው?**

የተለያየ አይነት ድምፆችን ማሰማትና የሰሙትን ድምፅ እንዲለዩ ማድረግ ፡፡

**ድምፅና ዝምታ**

ህጻናት ክብ ሰርተው ዙሪያውን እንዲሮጡ ማድረግ መምህሩ የማራከሻውን ድምፅ ሲያሰሙ ይሮጣሉ ድምፅ ሲቆም መሮጣቸውን አቁመው የሆነ ነገር ያደርጋሉ ፡፡

**የመዝሙሩን ስም ጥሩ**

የተማሩአቸውን መዝሙር መነሻ ድምፅ ማሰማትና መዝሙሩን እንዲለዩ ማድረግ ፡፡

**ድምፅና ቅርፅ**

ለተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎች የተለያየ ምልክት በመስጠት መምህሩ በሚያሳያቸው ምልክት መሰረት የመሳሪያውን አይነት እንዲያዩ ማድረግ ፡፡

የሰማሀውን ድምፅ አቅጣጫ ለይ ፡፡

አንድን ተማሪ አይኑን በጨርቅ በመሸፈን በተለያየ ኮርነር የተለያየ ድምፅን ማሰማትና የተጠየቀውን ድምፅ አቅጣጫ እንዲለይ ማድረግ ፡፡

**ተዛማጅ ድምፅ**

መምህሩ የሚያሰማውን ድምፅ ህፃናቱ አስመስለው እንዲያሰሙት ማድረግ ፡፡

**ከፍተኛና ዝቅተኛ ድምፅን መለየት**

ከፍተኛና ዝቅተኛ ድምፅን ደጋግሞ በማሰማት የዝቅተኛናየከፍተኛ ድምጾችን እንዲለዩ ማድረግ ፡፡

**ፍጥነትና ዝግታ**

የድምጾችን ፍጥነትና ዝግታ በተለያዩ ሙከራዎች ማስረዳት

ለምሳሌ- እንደ ኤሊ መንቀርፈፍን፣እንደ ፈረስ መጋለብን፣እንደወታደር መራመድን ወ.ዘ.ተ….

## 2. ሙዚቃዊ እንቅስቃሴ ፡-

ህፃናት እንደየ እድሜ ደረጃቸው ሙዚቃዊ እንቅስቃሴን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል

**ለምሳሌ፡-** ህፃናት መሰረታዊ ምቶችን ተከትለው መራመድን፣መሮጥ፣እጅ ማንሳትን፣ ማውረድን የመሳሰሉትን እነቅስቃሴ ማሰራት ፡፡

- ፈጣንና ዝግ ያለ ሙዚቃን በማድምጥ የመንቀሳቀስ ችሎታ እንዲኖራቸውና ተለዋዋጭ እንቅስቃሴ በሚያሰፈልገው ሙዚቃም ሙዚቃውን ተከትለው የመንቀሳቀስ ቸሎታ እንዲኖራቸው ማድረግ
- ቀላል የሆኑ ባህላዊ ውዝዋዜዎችን (ጭፈራዎችን)ደረጃ በደረጃ ማለማመድ ወ.ዘ.ተ…..

## 3. የሙዚቃ መሳሪያዎች ትውውቅ ፡-

የተለያዩ ሙዚቃ መሳሪያዎችን መተዋወቅ ህፃናት ለሙዚቃ መሳሪያዎች ያላቸውን ስሜት ከመቀስቀሱም ሌላ የእውቀት አድማሳቸውንም ያሰፋል ለዚህም ይረዳ ዘንድ በአካባቢያቸው የሚያገኙትንን ባህላዊና ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ማስተዋወቅና ከተቻለም የሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋቾችን በመጋበዝ ስለመሳሪያው ምንነትና አጨዋወት ለህፃናቱ እንዲያስረዱ ማድረግ ወ.ዘ.ተ….

## 4. መዝሙር ፡-

ከዋና ዋና የሙዚቃ ክንዋኔዎች ውስጥ መዝሙር በአፀደ ህፃናት ለህፃናት አካባቢያቸውን እንዲረዱ፣አካላዊና አእምሮቸው እንዲዳብር፣ሌሎች ትምህርቶችንም ለመማሪያነት እገዛ ያደርጋል።

**ለህፃናት መዝሙሮችን ማዘጋጀት**

ለህፃናት የሚሆኑ መዝሙሮችን ለመምረጥና ለማዘጋጀት ከፍተኛ ጥንቃቄን ይጠይቃል

- ✓ የመዝሙሩ ግጥም አጭርና ግልፅ መሆን
- ✓ የዜማው ሪትም ስሜትን ለመቀስቀስ መቻሉ
- ✓ የዜማው ድምፅ እርዝመት (interval)) የተመጠነ መሆን

- ✓ የመዝሙሩ ግጥም ከህፃናት ፍላጎት ጋር የተገናዘበ መሆኑ፤
- ✓ የግጥሙ ቃላት በቀላሉ ሊዘመሩ መቻላቸው፤
- ✓ መምህሩ ዜማዎችን ለመዘመር ፈቃደኛና ስሜት ሊሰጠው የሚችል መሆኑ፤
- ✓ የግጥሙ ትርጉምና ዜማው በትክክል መገናኘታቸው፤
- ✓ መዝመሩ በተለያየ አይነት ቅንብር መዋቡ፤
- ✓ በመጨረሻም መዝሙሩን ህፃናት በቃል ለመያዝ ያለው ቅለት ይገኙበታል፤

**የህፃናት ድምፅ**

ህፃን ልጅ ሶስት አይነት ድምፅ እንዳለው ይነገራል እነርሱም

ሀ. የመነጋገሪያ ድምፅ

ለ. የጨዋታ ድምፅ

ሐ. የዜማ ደምፅ ናቸው

የመነጋገርያ ደምፅ ንፁ-ህና ከፍተኛ የድምፅ ቃና(pitch) ሊያወጣ የሚችል ነው።እንዲሁም የዜማ ድምፃቸው ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን የጨዋታ ድምፅ ግን ቀጭን ሀይለኛና ጎርናና ነው ፡፡

**የመዝሙር ማስተማር ዘዴ**

አብዛኛዎቹ የህፃናት መዝሙሮች አጠናን በቅብብሎሽ ላይ የተመሰረተ ነው ህፃናቱ ከመምህራቸው የመያደምጧቸውን የግጥም የዜማና የሪትም ስልቶች በጥንቃቄ ማድመጥ መልስውም መደጋገምና ማስታወስ ልምድን እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል።

በቅብብሎሽ (round song) መዝሙር ላይ በመመስረት ሁለት አይነት የመዝሙርማስተማሪያ ዘዴዎች አሉ እነሱም የሚከተሉት ናቸው--

**1.መዝሙርን ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ በመደጋገም የማስተማር ዘዴ(hole )**

ይህን የማስተማር ዘዴ የመዝሙራቸው ግጥም አጭርና ግልፅ የሆኑ መዝሙሮችን ለማስተማር የምንጠቀምበት ሲሆን፡፡

1. በዚህ የማስተመር ዘዴ መምህሩ የመዝሙሮችን ሀረግ በመከፋፈል አያዘምርም
2. መምህሩ ሙሉ መዝሙሩን ብዙ ጊዜ በመደጋገም ህፃናቱ ጥልቅ ሀሳብ እንዲኖራቸው ያደርጋል
3. በመዝሙሩ ውስጥ ሊደረጉ የሚገባቸውንም እንቅስቃሴና የመሳሰሉትን ለህፃናቱ መዝሙሩን በመዘመር ያሳያል

**2. የመዝሙሩን ሀረግ (ስነኝ) በመከፋፈል የማስተማር ዘዴ**(phrase wise method)

ይህን የማስተማር ዘዴ የምንጠቀመው መዝሙሩ ለህፃናቱ ከባድ መስሎ ሲታየን ነው፡፡ የአዘማመር ዘዴውም በቅድሚያ መዝሙሩ በመምህሩ ሙሉ በሙሉ ከተዘመረ በሆላ ስንኝ በስንኝ በመከፋፈልና በማዘመር ላይ ያተኩራል

የአዘማመር ዘዴውም እንደሚከተለው ይሆናል ÷

- የመዝሙሩን ግጥም ማስተዋወቅ
- መዝሙሩን በሙሉ በመዘመርማስማት
- መዝሙሩ በሙሉ ከተዘመረ በኂላ አንዱን ስንኝ በመዘመር ማሰማት
- ህፃናቱ የሰሙትን ስንኝ እነዲያሰሙ ማድረግ
- የሚቀጥለውን ስንኝ ዘምሮ ማሰማት
- እንደገና ህፃናቱ የሰሙትን ስንኝ ደግመው እንዲዘምሩት ማድረግ ናቸው'

በዚህ አይነት ዘዴ እስከመጨረሻው መቀጠልና በመጨረሻስንኞቹን በመገጣጠም ዘምሮ ማሰማትና እንዲዘምሩ ማድረግ'

**መዝሙረን ለህፃናት በምናስተምርበት ጊዜ መገንዘብ የሚገቡን ነጥቦች**

- መዝሙር አስተማሪ የሚያሰተምረውን መዝሙር ከማስተማሩ በፊት ለራሱ መዝሙሩን በሚገባ ማወቅ ይገባዋል
- ህፃናት የተሳሳተ ድምፅ አለመጫወታቸውን መገንዘብ
- ያለአግባብ በጩሀት እንዳይዘምሩ መቆጣጠር
- የመዝሙሩን ዜማና ሪትም ጠብቀው እንዲዘምሩ ማድረግ
- የግጥሙን ቃላት በትክክል መያዛቸውን ማረጋገጥ
- ለመዘመር የተስተካከለ አቋምና አቀማመጥ እንዲኖራቸው ማድረግ
- መዝሙሩን በትክክለኛው ቴምፖና ዳይናሚክስ እንዲዘምሩ ማድረግ

**ቴምፖ**

ማንኛውም ሙዚቃ ወይም መዝሙር የተወሰነ ፍጥነት ወይም ዝግታ እንዲኖረው ሆኖ ይዘጋጃል ለዛና ጣእም ያለው ሙዚቃ ሊኖር የሚችለው የፍጥነትና የዝግታ ስልቶችን በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ሲቻል ነው።ቴምፖ ማለት የሙዚቃ ድምፅ ፍጥነትና ዝግታ መገለጫ ነው። የቴምፖ አይነቶቸ በአራት ዋና ክፍሎች ይመደባል፡፡

እነሱም ፡-

1. በጣም ዝግ ያለ
2. ዝግ ያለ
3. መካከለኛ ፍጥነት
4. በጣም ፈጣን ናቸው።

**ዳይናሚክስ**

ዳይናሚክስ ማለት የሙዚቃ ድምፅ  ዝቅ(ለስለስ) ከፍ  (ጮክ ) ለማድረግ የምንጠቀምበት ምልክት ነው'እንደሙዚቃው የዜማ አደራረስ ስልት ጣእም ለመስጠት ሲባል የተለያዩ የዳይናሚክስ ምልክቶች በስራ ላይ ውለዋል ከዚህ በመቀጠል ዋናዋናዎቹን የዳይናሚክስ ምልክቶችን እንተዋወቃለን ፡፡

| ምልክቱ | አለማቀፍ መጠሪያ ስም | ትርጉም |
|---|---|---|
| *P* | ፒያኖ(ፒያኖ) | ድምጽን በማለስለስ መዘመር |
| *F* | ፎርቲ (forte) | ድምጽን ጮክ በማድረግ መዘመር |
| < | ክሬሸንዶ(creshendo) | ቀስ በቀስ ድምፅን መጨመር |
| > | ዲክሬሸንዶ(dicreshendo | ቀስ በቀስ ድምፅን መቀነስ |

<u>**የማነቃቅያ ክለሳ ጥያቄዎች**</u>

1. የቅድመ መደበኛን የሙዚቃ ትምህርት ይዘቶችን ዘርዝሩ
2. የህፃናት የድምፅ አይነቶችን ጥቀሱ
3. መዝሙርን ለህፃናት በምናስተምርበት ግዜ መገንዘብ ከሚገቡን ጥንቃቄዎች ሶስቱን ጥቀሱ
4. ቁጥርን ለማስተማር ከሚረዱ የቅድመ መደበኛ መዝሙሮች የሁለቱን ስም ጥሩ
5. **k**ንቋ ለማስተማር ከሚረዱ የቅድመ መደበኛ መዝሙሮች የሁለቱን ስም ጥሩ

## አባሪ 1፡ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ናሙና መዝሙሮች

**የቁጥር መዝሙሮች**

**ቁጥር መቁጠር**

ቁጥር መቁጠር እወዳለሁ

ቁጥር መቁጠር እወዳለሁ

አንድ ሁለት ሶስት ከእንቅልፌ እነቃለሁ

አራት አምስት ከቁርሴንም እበላለሁ

ስድስት ሰባት ትምህርትቤት እሄዳለሁ

ስምንት ዘጠኝ ቁርሴንም እበላለሁ

አስር ሲሆን ወደቤቴ እሄዳለሁ፡፡

ወደቤቴ እሄዳለሁ፡፡

**የሳምንቱ ቀናት**

የሳምንቱ ቀናት እነማን ናቸው

ልጆች ልጆች እነወቃቸው

ሰኞ ማክሰኞ

እሮብ ሀሙስ አርብ እንማራለን

በአምስቱ ቀናት

ቅዳሜና እሁድ የእረፍት ነው

የሽርሽር የመዝናናት

በእረፍት ቀኔ እጫወታለሁ

ደግሞም ትምህርቴን አጠናለሁ

ደግሞም ትምህርቴን አጠናለሁ፡፡

**ትናንሽ ወፎች**

አንድ ሁለት ሶስት ትንሽ ትንሽ ወፎች

አራት አምስት ስድስት ትንሽ ትንሽ ወፎች

ሰባት ስምንት ዘጠኝ ትንሽ ትንሽ ወፎች

አስር ትናንሽፎች አስር ትናንሽፎች

**ሂሳብ መማር**

ሂሳብ መማር እወዳለሁ

ለጥር መማር እወዳለሁ

መደመር መቀነስ ችያለሁ

ሂሳብን መማር እወዳለሁ

ሂሳብን መማር እወዳለሁ

**የፊደል መዝሙር**

ህፃናት እንማር እንመራመር

ፊደልን ለማወቅ በርትተን እንጣር

ሀ እንደ ብርጭቆ ናት

ለ ወንበር ትመስላለች

መ መነፅር መሳይ ናት

ሸ ጭንቅላቷ ሪቫን

ቀ ጭንቅላቷ ሪቫን

ተ ግን እጇን ዘርግታለች

ተ ግን እጇን ዘርግታለች

**ፊደል**

ሀ ሁ ብለን ቆጥረን

ማንበብ መፃፍ በደንብ አውቀን

ለወላጆቻችን ደስታ

እንሆናለን ለሀገር አለኝታ (2)

**A B C D**

A B C D E F G

H I J K L M N O P

L M N O P Q R S T

U V W X Y Z X Y Z

**እኛ ሕፃናቶች እንማር**

እና ሕፃናች እንማር

እንማር እንመራመር

ሀኪሞች ለመሆን ለመርዳት ሰውን

እንማር እንማር እንመራመር

አዝማች

ሳይንቲስት ለመሆን በአየር ለላይ ለመብረር

እንማር እንማር እንመራመር

አዝማች

በጋራ ለመኖር አብሮ ለመስራት

እንማር እንማር እንመራመር

አዝማች

**የጤና መዝሙር**

ንፅህናዬን ጠብቂያለሁ

ንፅህናየን ጠብቂያለሁ ጠብቂያለሀ

በጣም ጥሩ ልብስ ለብሼአለሁ ለብሻኤለሁ

ፀጉሬን አበጥሬለሁ ጥፍሬን ተቆርጫለሁ

መሀረቤንም ይዤለሁ

ለሚመለከተኝ ደስ እላለሁ(2)

**የስሜት ህዋሳት**

አምስቱ አምስቱ የስሜት የስሜት

ህዋሳት ህዋሳት

አይን አፍነጫ ምላስ ጆሮና እጃቸን ናቸዉ

አይን አለኝ አያለሁ ጆሮ አለኝ እሰማለሁ

በአፍንጫዬም በአፍንጫዬም አሸታለሁ

በምላሴም በምላሴም አቀምሳለሁ

መዳሰሻ እጅም አለኝ እጅም አለኝ

የስሜት ህዋሴን አወቁልኝ

የስሜት ህዋሴን አወቁልኝ

## የስነምግባረር መዝሙር

**ወውሸታሙ እረኛ**

ዉሸታሙ አረኛ ዘወትር ልማደኛ

ቀበሮ መጣብኝ በጎቼን በላብኝ

እያለዘወትር ሲቀልድ ሲያስቸግር

በዚህ አድራጎቱ ደግሞም በዉሸቱ

ሁሉም ሰዉ ተማርሮ አንድ ቀን ቀበሮ

መጣና በድንገት በጎቹን በላበት

ዉሸታሙ አረኛ ዘወትር ልማደኛ

ESD

ኡ ኡ እያለ ወጣ የሚረዳው አጣ የሚረዳው አጣ

### ጥንቸል ጉረኛ

ጥንቸል ጉረኛ አፈረ

ኤሊ ትጉ ተከበረ

ጥንቸል ጉረኛ ሲነፋ ጉራ

ሮጦ በተስፋ ኤሊ አሸነፈ

ጻኖች እንስሳት አጨበጨቡ

ከኤሊ ብርታት ቀሰሙ ትምህርት።

### ጨዋታ

በአፀደ ሕፃናት ጨዋታ ሊሰጠው ይገባል ከፍተኛ ቦታ

ሊሰጠው ይገባል ከፍተኛ ቦታ

ጨዋታ ጨዋታ የእድገት ገበታ

ጨዋታ ጨዋታ የእድገት ገበታ

ለስብእና እድገት ምስረታ አስተዋፅኦ አለው ጨዋታ

አስተዋፅኦ አለው ጨዋታ

ለህፃናት አስደሳች የምስራች

ጨዋታ ጨዋታ ምንግዜም ጨዋታ

ጨዋታ ጨዋታ የእድገት ገበታ

### ወፊቷን እሆናለሁ

ወፊቷን እሆናለሁ

ከአየር ላይ እበራለሁ

ክዛፎቹ በላይ ወደላይ ወደ ላይ።

### ወላጆቼ

እናት አባቴን እወዳለሁ እህት ወንድሜን እወዳለሁ

በሰላም በፍቅር እኖራለሁ

ወላጆቼ ይመግቡኛል ወላጆቼ ያለብሱኛል

ወላጆቼ ያስተምሩኛል ወላጆቼ ያፈቅሩኛል

እናት አባቴን እወዳለሁ እህት ወንድሜን እወዳለሁ

በሰላም በፍቅር እኖራለሁ

### I have family

I have family they are so lovely

I have family I have family

My mother my father

My sister my brother

We all live together We all live together

### የቤት እንስሳት

የቤት እንስሳት መዘመር ይችላሉ አሁ ምንምን ይላሉ

ድመት ትዘምራለች ትጸነሳለች

ሚያው ሚያው ትላለች

ውሻስ ምን አለ ምን ምን አለ

ው ው ይላል አጥንትም ይበላል

ው ው ይላል አጥንትም ይበላል

አዝማች

ዶሮስ ምን አለች ምንምን አለች

ኩኩሉ አለች ከአጥር ለይ ዘለለች

ኩኩሉ አለች ከአጥር ለይ ዘለለች

አዝማች

ላምስ ምን አለች ምን ምን አለች

እምቧ እምቧ አለች ወተት ትሰጣለች

እምቧ እምቧ አለች ወተት ትሰጣለች

### እንስሳቶች ሁሉ

እንስሳቶች ሁሉ አንዳንዶቹ ይበራሉ

አንዳንዶቹ ይዘላሉ

አንዳንዶቹ ይራመዳሉ

እንስሳት ፍቅርን ይሸሉ(2)

### Head Shoulders

Head shoulder knees and toes

Knees and toes

Head shoulder knees and toes

Knees and toes

Eyes and ears and mouth and nose

Head shoulder knees and toes

Knees and toes

### Row your boat

Row row row your boat

Gently down the stream

Merrily Merrily merrily merrily

Life is but a dream

### Twinkle

Twinkle Twinkle little star

How I wonder what you are

Up above the world so high

Like a demand in the sky

Twinkle Twinkle little star

How I wonder what you are

### I am going home

Walk walk walk

La la la la la

Clap clap clap

La la la la la

Jump jump jump

La la la la la

Bye bye bye

I am going home

Bye bye bye I am going home

### This is the way

1.This is the way I wash my face

wash my face wash my face

This is the way I wash my face

So early in the morning

1. this is the way I brush my teeth

brush my teeth brush my teeth

this is the way I brush my teeth

So early in the morning

2. This is the way I comb my hair

Comb my hair comb my hair

ESD

This is the way I comb my hair

So early in the morning

3. This is the way I put on my cloth

Put my on cloth put my on cloth

This is the way I put on my cloth

So early in the morning

4. This is the way we go to school

Go to school go to school

This is the way we go to school

So early in the morning

## ደስ ብሎናል

ደስ ብሎናል ደስ ይበላችሁ

መዋእለ ሕፃናት ጨረስንላችሁ

ለመምህሮቻችን እናቅርብ ምስጋና

እኛን ለዚህ ጊዜ አድርሰዋልና

በዚህ ቆይታችን በሶስቱ አመት

በደንብ ተምረናል ጠቃሚ ትምህርት(2)

በክረምቱ ወራት በእረፍታችን

እዚህ የተማርነው እንዳይረሳን

የቤተሰብ ድጋፍ እንዳይለየን

## እኛ ሕፃናቶች

እኛ ሕጻናቶች መማር እንወዳለን

መጫወት መደሰት ሀሌም እንሻለን

ላጫወተን ቀርቦ ለተንከባከበን

ወዳጅ ስለሆነን ፍቀርን እንሰጣለን(2)

## አባሪ 2፡- የየምዕራፎቹ ጥያቄዎች መልስ

**ምራፍ 1**

1. ድምፅ
2. ሀ. ቅኝት ለ. አይነት ሐ. ቃና መ. ቆይታ ሠ. መጠን
3. ከፍተኛና ዝቅተኛ ድምፅን ያመላክታሉ
4. በአራት ይከፈላሉ እነሡም ሀ. ሶፕረራኖ

   ለ. አልቶ

   ሐ. ቴነር

   መ. ቤዝ ናቸው፡፡

**ምራፍ 2**

1. ኖታ
2. አምስት መስመርና አራት ክፍት ቦታዎች
3. ሰባት ናቸው እነሡም ዶ ሬ ሚ ፋ ሶል ላ ሲ ዶ ናቸው፡፡
4. ሐሰት
5. አውነት
6. እውነት
7. እውነት
8. እውነት

**ምእራፍ 3**

1. ስምንት ናቸው
2. ሀ. ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ

   ለ. ነርሲስ ናልባንድያን

3. ሀ. ሞዛርት ለ. ቤቶቨን

**ምራፍ 4**

1. በሶስት ይከፈላሉ 1. የትንፋሽ 2. የክር 3. የምት ናቸው፡፡
2. ሀ. ዋሽንት ለ. መለከት ሐ. ጡሩንባ
3. ሀ. ክራር ለ. ማሲንቆ
4. ማጨብጨብያ ጣውላ፤ ከበሮ፤ማራካሻ፤የምት ዱላ ወ.ዘ.ተ...

**ምዕራፍ 5**

1. በባለ አምስት ድምፅ
2. አራት ናቸው እነሡም 1. ትዝታ ቅኝት
   2.ባቲ ቅኝት
   3.አንቺሆዬ ቅኝት
   4.አምባሰል ቅኝት ናቸው፡፡

**ምዕራፍ 6**

1. ሶልፌጆ ማለት የሙዚቃን ኖታ የማንበብ የመፃፍና የመስማት ክህሎትን የማዳበርያ ትምህርት ነው፡፡
2. የርምጃ ምት፤ የሩጫ ምት፤ የመንጠር ምት ናቸው፡፡

**ምዕራፍ 7**

- ሙዚቃ ህፃናት በስነ ስርአት ታንፀው እንዲያድጉ ይረዳል
- ሙዚቃ የህፃናትን የkንቋ ችሎታቸውንና ንግግራቸውን ያሻሽላል
- ሙዚቃ ለህፃናት አካላዊና አእምሮአዊ እድገት ከፍተኛ እገዛ አለው፡፡
- ሙዚቃ በቅድመ መደበኛ ህፃናት ሌሎች ትምህረርቶችን ለማስተማርያነት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡

**ምዕራፍ 9**

1. ሀ. ማድመጥ

   ለ. ሙዚቃዊ እንቅስቃሴ

   ሐ. የሙዚቃ መሳርያዎች ትውውቅ

   መ. መዝሙር ናቸው፡፡

2. ሶስት ናቸው እነሡም ሀ. የጨዋታ ድምፅ

   ለ. የንግግር ድምፅ

   ሐ. የዜማ ድምፅ ናቸው፡፡

3. ሀ. ያለአግባብ በጩኸት እንዳይዘምሩ ማድረግ

   ለ. የተሳሳተ አተነፋፈስ እንዳይጠቀሙ መቆጣጠር

   ሐ.የግጥሙን ቃላት በትክክል ማወቃቸውንና መስማታቸውን ማረጋገጥ

   መ. ለመዘመር የተስተካከለ አቀማመጥና አቋም መያዛቸውን ማረጋገጥ …

4. ሀ. ትናንሽ ወፎች ለ. ቁጥር መቁጠር እወዳለሁ

5. ሀ. A B C D ለ. ሕፃናት እንማር

## ዋቢ መፅሀፍት (Referances)


- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ሲለበስ
- የአንደኛ ደረጃ የሙዚቃ ማስተማርያ መፅሀፍ
- Gerowing with music
- The enjoyment of music
- Old favorites for allages song book